# የውጭ ጉዳይ ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ
# (የስልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የስልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች

ዶ/ር እድሪስ የባ

ዶ/ር መብራቱ ታፈሰ

ዶ/ር ሞሳ ሁሴን

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኊላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ኃይሌ

ግራፊክስ፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ. ም

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


ማውጫ........................................................................................................................ iv

መግቢያ........................................................................................................................ vi

የስልጠና ሞጁሉ ዓላማ...................................................................................................viii

የስልጠና ሞጁል አጠቃቀምና አቀራረብ...............................................................................viii

ምዕራፍ አንድ................................................................................................................ 1

1. የሙስና ወንጀል ምንነት ................................................................................................ 1

1.1 መግቢያ ................................................................................................................ 1

1.2 የሙስና ወንጀል ምንነት ................................................................................................ 1

1.3 የሙስና ዓይነቶች ....................................................................................................... 3

*1.3.1 ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption) ..........................................................................3*

*1.3.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption)..........................................................................4*

*1.3.3 ስርዓታዊ ሙስና (Systemic Corruption) ...................................................................6*

*1.3.4 ፖለቲካዊ ሙስና (Political corruption).......................................................................7*

1.4 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት .......................................................................................7

*1.4.1 የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት ...................................................................................8*

*1.4.2 የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት ........................................................................8*

*1.4.3 የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም.....................................................................................8*

*1.4.4 በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር......................................................................9*

*1.4.5 ድንበር ተሻጋሪነቱ ................................................................................................10*

1.5 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ....................................................10

1.6 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ....................................................10

1.7 የማጠቃለያ ጥያቄዎች ..............................................................................................18

1.8 ማጠቃለያ .............................................................................................................19

ምዕራፍ ሁለት..............................................................................................................20

2 በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት፣ ብልሹ አሰራሮች እና ጉዳቶች.............20

2.1 መግቢያ ...............................................................................................................20

2.2 በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት እና ብልሹ አሰራሮች......................21

*2.2.1 የሙስና ስጋት ..................................................................................................21*

*2.2.2 ለውጭ ጉዳይ ዘርፍ የተሰጡት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት .........................................22*

*2.2.3 በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች...........................................23*

2.2.3.1 የሥነ ምግባር ክፍሎችን ከማደራጀት አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች .......................23

2.2.3.2 ተጠያቂነትንና ግልፅነት ከማስፈን አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች ...........................24

2.2.3.3 አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች 26

2.2.3.4 የንብረት አስተዳደር ስርአትን ከመዘርጋት አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች.................26
2.2.3.5 የግዥ አስተዳደር ስርአትን ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች.....................27
2.2.3.6 የሰው ሃብትን በአግባቡ ከማስተዳደር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች ........................28
2.2.3.7 የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓትን ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች......29
2.2.3.8 የፕሮጀክቶች አስተዳደር ሥርዓትን ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች.........30
2.2.3.9 የኦዲትና ቁጥጥር ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች ...................32

2.3 ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች.......................................................................35
*2.3.1 መግቢያ.......................................................................................35*
*2.3.2 የሀገር ገጽታ ጉዳቶች.........................................................................35*
*2.3.3 የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እና የልማት ትብብር ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች.......................37*
*2.3.4 በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራው) ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተጽዕኖዎች..................39*
*2.3.5 የውጭ ዕዳ መጨመር እና የፋይናንስ አለመረጋጋት ..............................................41*
*2.3.6 ሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች መስፋፋት ......................................43*

ምዕራፍ ሶስት..........................................................................................47

3. በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና መከላከያ ስልቶች ...................................................47

3.3 መግቢያ...........................................................................................47
3.4 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት .....................................................................49
3.5 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን.......................................................................50
*3.5.1 ግልጽነት .....................................................................................50*
*3.5.2 ተጠያቂነት....................................................................................51*

3.6 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ.................................................................52
3.7 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ .................................................................52
3.8 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል..........................................................53
3.9 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ.................................................54
3.10 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር...........................................................54
3.11 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት ....................................................55
3.12 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል ......................................................................55

ዋቢ መጽሐፍት .........................................................................................58

# መግቢያ

በከፍተኛ ንቃት እና ጥንቃቄ ከሙስና አደጋዎች መጠበቅ ካላባቸው ስትራቴጂካዊ ከሆኑ ዘርፎች ውስጥ አንደኛው የውጭ ጉዳይ ነው፡፡ የሀገራችንን ሉዓላዊነት፣ ብሄራዊ ክብርና ጥቅሞች ከማስከበር አንጻር ዘርፉ የተሰጠው ህጋዊ ኃላፊነት እና ይህንኑ ለመወጣት ከሚያንቀሳቅሰው ሀብት በተጨማሪ ይህንን ተቋም ለማሳት ከውጭ ኃይላት የሚቀርቡ ማታላያዎች አንጻር፣ የተለያ ትኩረት እና ጥንቃቄ የሚፈልግ ዘርፍ ነው፡፡ በተለይ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ እንደ አንጋፋ እና ትውልዶችን አልፎ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ገጽታና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ተሰሚነት እና ተጽዕኖ በዘለቂነት እንዳጸና ተቋም በዚያ ልክ የተዋጀ የራሱ የሙስና መከላከል ስልቶች እና ዘዴዎች ያስፈልጉታል፡፡ ይህ ደግሞ ከዘርፉ ተፈጥሮ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ሁለት ተቃርኖ ያላቸው ገጽታዎችን ያሳየናል፡፡

የመጀመሪያ እና ዋነኛው ዘርፉ ከፊሉን ስራዎቹን የሚሰራው በሚሲዮኖቹ በኩል በውጭ ሀገራት የህግ እና አስተዳደረዊ አውዶች ውስጥ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ሀገራችንን መቀመጫ ያደረጉ እጅግ የበዙ እና የተለያየ አቅም እና ፍላጎት ካላቸው ሀገራት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት የተያያዙ ብሄራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ኃላፊነቶችን ይወጣል፡፡ በነዚህ ውስብስብ አውዶች በዘለቂነት ስኬታማ ስራዎችን መስራት ከፍተኛ የሰው እና የሀብት አቅም ይጠይቃል፡፡ ሀገራችን ካላት ሀብት ለዚህ ዘርፍ የሚመደበው ጉልህ ቢመስልም፣ ከሚያስፈልገው እና ዘርፉ ከሚሰራበት አውድ አንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ በእጅግ በጣም ዝቅተኛ ወጭ የላቀ ውጤት ያገኘችበት ነው፡፡ ካለን ስትራቴጅካዊ ጥልቀት ከሚሰጡን ምክንያቶች እንደ የጥንታዊ ስልጣኔ፤ የአድዋ ድል ባለቤትነት እና የአፍሪካ ዲፕሎማሲ ማዕከል ከመሆናችን ጋር በአነስተኛ ወጭ ሁሉንም ሃያላን ሀገራትን የፖሊሲ ነጻነታችንን ባስከበረ መልኩ አስተናግደን፣ የአባይን ሃይድሮፖለቲካ እንዲሁም የአፍሪካ ቀንድ እና ቀይ ባህር የጅዖፖለቲካ ተጽዕኖዎችን ተቋቁመን፣ ዋነኛ ቀጠናዊ ሰላም አስከባሪና የደህንነት ኃይል ሆነን መዝለቃችን ውስጥ የውጭ ጉዳይ ዘርፉ ቀዳሚና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በተለይ አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ሀገሪቱ ከምትከተለው ዜጋ ተኮርና ቅድሚያ ለጎረቤት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አንጻር ዘርፉ የዜጎቹንና የሀገሪቱን ጥቅሞች ከማስጠበቅ አኳያ ያሉ እድሎችና ተግዳሮቶችን መለየት በዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ያግዛል፡፡ በዚህ በአነስተኛ ወጭ የላቀ ውጤት በዘላቂነት ሲያስመዘግብ በኖረ ዘርፍ ውስጥ የተቋሙን መልካም ስራ እና ስም እንዲሁም የታታሪ ሰራተኞቹን ስራ በማይነካ መልኩ ምን ዓይነት የጸረ ሙስና

ትግል ስልቶች መጠቀም ይበጃል ለሚለው ጥያቄ ተገቢ መልስ መርምሮ መፈለግ ለተሳካ ጸረ ሙስና ትግሉ ወሳኝ ነው።

ሁለተኛው የዚህ የብሔራዊ ገጽታ ምልክት የሆነን ዘርፍ ዕይታ የሚያጎድፉ እና መልካም ስሙን የሚያጠለሹ አልፎም ተርፎም ብሔራዊ ደህንነትን እና ጥቅሞችን ለአደጋ የሚያጋልጡ የሙስና ስጋቶች አሉ። የዘርፉን ልዩ ባህርያት ማዕከል ያደረጉ የሚሲዮኖች ግንባታ ፕሮጀክቶች አስተዳደር ህግ፣ የሰው ኃብት አስተዳደር እንዲሁም የግዥ እና የፋይናንስ ህጎችና ግልጽ ማዕቀፎች ያለ መደንገግ አደገኛ ክፍተቶችን ሊፈጥር ይችላል። እነዚህ ክፍተቶች ለጥቂት ሙሰኞች ቀዳዳ በመስጠት የሀገር እና የተቋምን ስም የሚያጠፉ ስራዎች እንዲሰሩ መንገድ ይከፍታሉ። እነዚህ ደግሞ በአንጻሩ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶችና እና የልማት ትብብሮች እንዳያድጉ ወይም እንዲሸሹ፣ ዳያስፖራው ተገቢውን ድጋፍ እንዳያገኝ እና ለአሉታዊ ተጽዕኖዎች እንዲጋለጥ፣ ለውጭ ዕዳ መጨመር እና የፋይናንስ ያላመረጋጋት፣ እንዲሁም ሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች መስፋፋት እና መሰል አደጋዎች ሊያጋልጥ ይችላል።

በአጠቃላይ ዘርፉ የተሰጠውን ብሄራዊ ኃላፊነት በቀጣይነት እና በውስብስብ እና ተለዋዋጭ ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴዎች አውዶች ውስጥ በልህቀት እንዲፈጽም፣ የሙስና ተጋላጭነቱን ከራሱ ከዘርፉ አውድ በማጥናት፣ በመተንተን እና የመፍትሄ ስልቶችን እና ዘዴዎችን በማመንጨት፣ ቅድሚያ መስጠት እና መተግበር ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር የዘርፉ ሃላፊዎች ከፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በጥብቅ ቁርኝት በመስራት ዘርፉ ውስጥ በመሆን የማይታዩ ስጋቶችን እና ክፍተቶችን ለመለየት እንዲሁም በሌሎች አውዶች ተተግብረው አመርቂ ውጤት ያስገኙ ስልቶችን እና ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለመጠቀም ያስችላቸዋል።

ይህ የስልጠና ሞጁልም የተዘጋጀው ይህንኑ ጥረት ለማገዝ ሲሆን በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመፈተሽ የተቋሞቹን (የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር፣ በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት) አመራሮችንና ሰራተኞችን ስነ-ምግባር ለማጎልበትና ሙስናን የመከላከል አቅማቸውን ማጠናከር ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

**የስልጠናው ተተኳሪዎች**

በዚህ ሞጁል በውጭ ጉዳይ ዘርፍ (ማለትም በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር፣ በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት) ያሉ አመራሮችንና ሰራተኞች የሚሰለጥኑበት የስልጠና ሞጁል ነው፡፡

## የስልጠና ሞጁሉ ዓላማ

**አጠቃላይ ዓላማ፡**

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ሠልጣኞች የተቋሙን የአሰራር ስርዓት በመገንዘብ በዘርፍ የሚስተዋሉትን የሙስና ስጋቶችናተጋላጭነትን በመለየትና ቀድመዉ ለመከላከል የሚያስችላቸዉን ልቶችን በመገንዘብ ይተገብራሉ ፡፡

**ዝርዝር ዓላማዎች፡-**

ሠልጣኞች ይህን ሥልጠና ካጠናቀቁ በኋላ የሚከተለትን ተግባራት ያከናውናሉ፥

- ☑ ስለ ሙስና ጽንሰ ሃሳብ ፣ አይነቶችና መገለጫቸው ፣መንስኤወች እንዲሁም ስለሙስና ወንጀል ምንነት ይገነዘባሉ
- ☑ ሙስና ሊያስከትላቸው የሚችሉ ጉዳቶችን እና የመከላከያ ስልቶችን በጥልቀት ይፈትሻሉ
- ☑ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ወንጀሎችን በመፈተሽ የሙስና ስጋት ይዘረዝራሉ፡፡
- ☑ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ይለያሉ ፡፡
- ☑ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳቶች ያብራራሉ፡፡
- ☑ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶችን በመለየት ይተገብራሉ፡፡

## የስልጠና ሞጁል አጠቃቀምና አቀራረብ

ይህ ሞጁል ግቡን ይመታ ዘንድ የተለያዩ ሰልጣኝ ተኮር የመወያያ መልመጃዎችንና ተግባራትን በማቅረብ የሚከተለት ዋና ዋና ዘዴዎችን ይጠቀማል፡፡

☆ የመነሻ ተግባር/ማነቃቂያ ጥያቄዎች/ሀሳብ ማፍለቅ (Brainstorming)

- ☆ አጫጭር ገለጻ (Presentations)
- ☆ የቡድን ወይይት (Group Discussions)
- ☆ አስረጅ ናሙና (Case Studies)

ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ፡ **12 ሰዓት**

**ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፡-** ማስታወሻ ደብተር፣ እስክሪብቶ፣ ማርከር፣ ፕሮጀክተር፣ ላፕቶፕ እና የመሳሰሉት።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. የሙስና ወንጀል ምንነት

### 1.1 መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀበል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው። ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል። በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምእራፍ ነው።

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኂላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትንና የሙስና አይነቶችን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

**የዚህ ምዕራፍ ስልጠና የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ**

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 1:30 ሰዓት ነው።

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ።

### 1.2 የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው። ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም

የተባበሩት መንግስታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሰጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ “… የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል…” በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል። የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎችሰ መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን። ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ።

## 1.3 የሙስና ዓይነቶች

የሙስና ወንጀሎችን አይነት የበለጠ ለመረዳ በሁለት ተከፍለው ቀላል እና ከባድ ወይም (petty and grand) በሚል ለመረዳት መሞከር ይቻላል። በዚህም መሰረት ቀላል ሙስና በታችኛው ሀላፊነት እርከን ወይም በዝቅተኛ መጠን የሚፈፀሙትን በሚመለከት ሲሆን ከባድ ደግሞ በከፍተኛ ስልጣን እርከን ወይም በብዙ መጠን የሚፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ነው። ከባድ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) የሚችል ነው።

### 1.3.1 ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው። ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው።

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው። መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት

አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው። መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው።

**የዝቅተኛ ሙስና መገለጫዎች**

- ☞ በመንግስትና በህዝብ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ጉቦ መቀበል፣
- ☞ የግብር ምደባን በጉቦ እና በመደለያ በመስራት ያልተመጣጠነ የገቢ ግብር ምደባ ማካሄድ፣
- ☞ በልዩ ልዩ የቢሮ መሳሪያዎች እና በተሽከርካሪ ግዥ እና ጥገና ወቅት በሚደረግ ማጭበርበር /ሰነድችን በመሰረዝና በመደለዝ/
- ☞ በልዩ ልዩ የወጪ እና ገቢ ሰነድች ላይ ማጭበርበር /ሰነድችን በመሰረዝ፣ በመደለዝ እና በማጥፊት፣
- ☞ በልዩ ልዩ የግንባታ የጥገና እና የአገልግለት ጨረታዎች የማጭበርበር ተግባር በመፈፀም፣
- ☞ ህገወጥ የትምህርት እና የህክምና ማስረጃ በመስጠት ወይም በትምህርት ወይም በስልጠና የተገኘን ሙያ ህገወጥ በሆነ መንገድ /ህዝብን ሉጎዳ በሚችል መልኩ/ በመጠቀም የሚፈጸም ነው።

አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው።

### 1.3.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption)

ይህ የሙስና አይነት መጠነ ሰፊ የሆነ የህዝብና የመንግስት ሀብት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚመዘበርበትና የሚዘረፍበት የሙስና ወንጀል ሲሆን በአፈጻጸሙም ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላት እና ሀብትና ዕውቀት ያላቸው ግለሰቦች የሚሳተፉበት ነው። ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስልት በሚሉዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ነው።

ይህ የሚሆነው ፈጻሚዎቹ ከፍተኛ ስልጣን፣ እውቀትና ሃብት ያላቸው በመሆናቸው ድርጊቱን በረቀቀ ስልት የመፈጸምና ሚስጢራዊ የማድረግ አቅም ስላላቸው ነው።

በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የፌዳራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/9/ መሠረት ከባድ /ከፍተኛ/ የሙስና ወንጀል የሚባሉት ከዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚለዩባቸው ነጥቦች የሚከተለት ናቸው፦

1. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያካተቱ የሙስና ወንጀልች /ለምሳሌ የገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች፣ ባንኮች፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ የተሰማሩ መሥሪያ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ የደህንነትና የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ወዘተ/ ወይም፣
2. የመንግሥት ባለሥልጣናትን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች /በምርመራ ሂደትም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቁ፣ በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ የሚያስከትሉት ውጤት ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን ወይም፣
3. በአገር ሉአላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ጸጥታ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀልች በከፍተኛ ሙስና ደረጃ የሚፈረጁና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው።

**ከባድ /ከፍተኛ/ የሙስና ወንጀልመገለጫ መንገዶች**

ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption) በዋነኛነት በጉቦ፣ በማጭበርበርና በዝርፊያ የሚገለጽ ሲሆን ለአብነት ያህል እነዚህ መገለጫዎች በሚከተሉት ተግባራት ይከሰታሉ፡

- በአገር ደረጃ በሚከናወኑ የጦር መሳሪያዎች ላይ በሚፈጸም ህገወጥ ግዥ /እንደጦር አውሮፕላኖች፣ ታንኮች መርከብ እና ልዩ ልዩ ከባድ መሳሪያዎች በመሳሰሉት/፣
- ህገወጥ በሆኑ ጨረታዎች በሚፈጸሙ ከፍተኛ የግንባታ ውሎች /ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግንባታዎች፣ ከፍተኛ የመስኖ እና የመጠጥ ውሃ ግድብ ግንባታዎች፣ የመንገድ ሥራዎች፣ በከባድ ፋብሪካዎች ግንባታዎች/
- ልዩ ልዩ ለአገር ውስጥ ምርት አገልግለት የሚውሉ እንደማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣ መድሃኒቶች፣

- የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች እና የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች ለመግዛት በሚፈጸሙ ህገወጥ ግዥዎች፣
- ከፍተኛ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦቶች ላይ በሚፈጸም ህገወጥ ግዥዎች እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

**የከፍተኛ ሙስና ምሳሌ**

በመከላከያ ኢንዱስትሪወች አካል በነበረዉ ብረታብረት እና ኢንጂኔሪንግ ኮርፖሬሽን (MetEC) ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ትራንስፎርሜሽን ከፍትኛ ሚና ይጫውታል በመንግስት የተቋቋመ ነው። ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ እየተካሄዱ ባሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተሳትፏል። ለምሳሌ ለህዳሴ ግድብ የሀይድሮሊክ ክፍሉን ለመገንባት፤ 10 ግዙፍ የስኳር ፋብሪካዎችን ለመገንባት፤ የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካ ለመገንባት በተጨማሪም ትራንስፎርመር፤ተርባይን፤ከባባድ መኪናዎችን እና ሌሎችንም ኢኪውፕመንት የማምርት ስራ ከተሰማራባቸው ስራውቸው ውስጥ ይገኝበታል። ይሁንና ትቋሙ የታለመለትን ግብ ማሳካት አልቻለም። አንዱንም የስኳር ፍብሪካ (ለአንዳንድ የስኳር ፕሮጀክቶች እስከ 90 ፐርሰንት ክፍያ ተከፍሎታል) እንዲሁም የማዳበሪያ ፋብሪካ (11 ቢሊዮን ብር አጠቃላይ ክፍያ ተከፍሎት ፕሮጀክቱ 40% ላይ ቆሟል) ሳያጠናቅቅ ቀርቷል። ለግድቡ ኤሌክትሮመካኒካል ክፍል ለወሰደው ኮንትራት ዉል 65% ክፍያ (ከአጠቃላዩ 26 ቢሊዮን ብር ወይምም 776 ሚሊዮነ ዩሮ) የወሰደ ቢሆንም የተሰራው ስራ ግን ከ 25 አይበልጥም..... በዚህ መልኩ በተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብር ተመዝብሯል።

**ምንጭ**: Solomon Goshu (January 28, 2019) Recent Corruption Crackdown in Ethiopia: What Can We Learn From It?. International Anti-Corruption Conference (IACC).

### 1.3.3 ስርዓታዊ ሙስና (Systemic Corruption)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና

ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡ ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic corruption ) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) የሚችል ነው፡፡ ሙስና ስርአታዊ ከሆነ የሀገርን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለማስፈጸም ሙስናን ዋነኛ መሳሪያ አድርጎ ይጠቀማል፡፡ በዚህም ምክኒያት የሀገርን ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ ስልጣን ለተቆጣጠረው አካል ወይም ቡድን ፍላጎት ማስፈጸሚያ ያደርጉታል፡፡

### 1.3.4 ፖለቲካዊ ሙስና (Political corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዱሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

## 1.4 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ ሆነ ወንጀል፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያደርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ

የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ:: የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፤

### 1.4.1 የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ:: በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ:: የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል::

### 1.4.2 የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል :: ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል:: ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል:: ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል:: በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል::

### 1.4.3 የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት

ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 1.4.4 በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.4.5 ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ። በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኮን ሊጊሊግል ይችላል። ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል።

## 1.5 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል። በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው።

## 1.6 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

### 1.6.1. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይምሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛውም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራውን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያው ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛውም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባው ውል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተው ሰው ላይ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበውን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል።

### 1.6.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛውም ፦የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤

ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፡ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ውል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ውል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠውን ጥቅም ወይም የሚረዳ ውሳኔ፣ ለሌላ ሰው ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፡ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደው አሠራር ውጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛው በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣው ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.6.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.6.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰው  የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኘው ከነበረው ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘው ወይም ሲያገኘው ከነበረው ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.6.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለው ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራው ምክንያት ያወቀው ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነውን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘውን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለውን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራውን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኂላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነው፤ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤ በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.16 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.17 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛውም ሰው ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ለማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሌላ ሰው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለው ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል። በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠይቅም።

### 1.6.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛውም ሰው አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባው ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

### 1.6.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛውም ሰው ለራሱ ማናቸውንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናውን ሰው ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለው ነገር፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣ ያገናኘ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

### 1.6.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን

መስሎ በመቅረብ፤ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል።

### 1.6.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል።

ሰጭውም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል።

### 1.6.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል።

### 1.6.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ

ሰው አገልግሎት ያዋለ፣መውሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መገኘቱን ወይም መደበቁን እንጂ መውሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡

### 1.6.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነው፡፡

### 1.6.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

## 1.7 የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፣ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፣
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል” ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

## 1.8 ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2 በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት፣ ብልሹ አሰራሮች እና ጉዳቶች

## 2.1 መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የሙስና ስጋትና ብልሹ አሰራሮች ጽንሰ ሀሳቦች እንዲሁም ስጋቶች ከውጭ ጉዳይ ዘርፍ አኳያ በሁለት ዋና ዋና ትምህርት ክፍሎች ቀርቧል፡፡ በክፍል አንድ የሙስና ስጋት እና ብልሹ አሰራሮች ቀርቧል፡፡ በክፍል ሁለት የውጭ ጉዳይ የሚፈጸሙ ሙስና ሊያደርስ የሚችላቸው ጉዳቶች ተዳሷል፡፡ በምዕራፉ መግቢያ፣ ማጠቃለያ እና ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎችም ተካቷል፡፡

**የምዕራፉ ዓላማዎች**

ሰልጣኞች ይህን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ፣

- ስለ ውጭ ጉዳይ ዘርፍ  አጠቃላይ ተልዕኮ ይገልጻሉ
- በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስለሚስተዋሉ የሙስና ስጋት ይገነዘባሉ
- በዘርፉ ስለሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች እና የሙስና ክስተቶች በጥልቀት ይተነትናሉ
- ሙስና ሊያስከትላቸው የሚችሉ ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ
- ሙስና እንዴት የሀገርን ገፅታ በማበላሸት የሀገርን ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ እና ተሰሚነት እንደሚቀንስ ያስረዳሉ
- ሙስና እንዴት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች እና የልማት ትብብሮችን ሊያሸሽ እና ሊያደርቅ እንደሚችል በዝርዝር ያስረዳሉ
- ሙስና በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ዳያስፖራው ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ ተንትነው ያቀርባሉ
- ሙስና የሚያስከትላቸውን የውጭ ዕዳ በመጨመር እና የፋይናንስ ያላመረጋጋት እንዴት የሉዓላዊ የፖሊሲ ነጻነትን  እንደሚጎዳ በዝርዝር ያስረዳሉ
- ሙስና የሚያስከትላቸው ሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች እንዲስፋፉ እና ብሄራዊ ደህንነታችንና ጥቅሞቻችን እንዲሁ ሀገራዊ ህልውና ለአደጋ እንዲጋለጡ የሚያደርጉበት ቢሆኖዎች ያቀርባሉ፡፡

**የዚህ ምዕራፍ ስልጠና የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ**

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ <u>7፤00</u> ሰዓት ነው፡፡

## 2.2 በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት እና ብልሹ አሰራሮች

በዚህ ክፍል ስር የሙስና ስጋትና ብልሹ አሰራሮች ጽንሰ ሀሳቦች ከውጭ ጉዳይ ዘርፍ አኳያ በሶስት ዋና ዋና ትምህርት ንዑስ ክፍሎች ቀርቧል። በንዑስ ክፍል አንድ የሙስና ስጋት ምንነት ተዳሷል። በንዑስ ክፍል ሁለት የውጭ ጉዳይ ዘርፍ በህግ የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር ተካቷል። በንዑስ ክፍል ሶስት በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ- ሙስና ኮሚሽን በ2015 ባካሄደው የሙስና ዳሰሳ ግኝትን መሰረት አድርጎ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚታዩ ዋና የሙስና ስጋቶችና የተጋላጭነት ምንጭነች ቀርቧል።

### 2.2.1 የሙስና ስጋት

**መነሻ ተግባር**

ውድ ሰልጣኞች የሙስና ስጋት በማንኛውም ተቋም በሁሉም ደረጃዎች የሚገኝና የሚኖር ነው። የሙስና ስጋት እንደየ ሀገሩና የተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታና ጊዜ ይለያያል። በቡድን (የቡድኑ አባላት እንደተሳታፊው ብዛት ከ3-7 ሊሆኑ ይችላሉ) በመሆን የተቋማችሁ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ያሉ የሙስና ስጋቶችና የተጋላጭነት ምንጭች በመለየት በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የስጋቶቹ ምንጭ ላይ ተወያዩበት።

የሙስና ስጋት ማለት የአንድ ተቋም ዓላማ እንዳይሳካ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትል ቀጣይነት ያለው ውስጣዊና ውጫዊ ክስተት ማለት ነው። እንደማንኛውም ተቋም ይህ ስጋት በውጭ ጉዳይ ዘርፍ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችል ክስተት ነው። በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ በሚካሄዱ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሙስና ስጋቶች ይገኛሉ። እነዚህ ስጋቶች በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ውስጥ ሊከሰቱ ይችላሉ። እነዚህ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን በሳይንሳዊ መንገድ በመለየት እና በመተንተን የሙስና የመከሰት ስጋቶችንና እድሎችን በእጅጉ መቀነስና በብቃት መቆጣጠር ያስፈልጋል።

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ በሚካሄዱ የሙስና ስጋቶች/ተጋላጭነት መለያ፣ መተንተኛና መገምገም ጥናትና ስራ ላይ ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ? ከተሳተፉችሁ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና የሙስና ስጋቶችና ለሙስና ተጋላጭነትን የሚጨምሩ ድርጊቶች እነማን ናቸው? እነዚህን ስጋቶች ከአጭር፣ መካከለኛ እና ረጅም ጊዜ አኳያ የሀገር መልካም ስምን ከማጠልሸትና ዓለም አቀፋዊ ተሰሚነት ከመቀነስ፣ የውጪ ዕርዳታ እና ቀጥተኛ

ኢንቨስትመንት ከመቀነስ፣ በውጭ ከሚኖሩ ዜጎች መብትና ክብር ከማስጠበቅ የውጭ ዕዳ መጨመር እና የፋይናንስ አለመረጋጋት፣ ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎችን፣ ሽብርተኝነትን እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ከማበረታታት፣ የተዛቡ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነቶችን ናየሀገር ሀብት እንዲኮበልልና እንዲዘረፍ ከማበረታታት አኳያ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የስጋቱን ደረጃ ላይ በቡድን በመወያየት ከታች ባለው ቦታ ላይ ሃሳቦችን ከገለፃችሁ በኋላ የቡድናችሁን ዋና ዋና ሃሳቦችን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

### 2.2.2 ለውጭ ጉዳይ ዘርፍ የተሰጡት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት

የቡድን ውይይት

ውድ ሰልጣኞች ለውጭ ጉዳይ ዘርፍ ከተሰጡት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ ጥቂቶቹን ዘርዝራችሁ አተገባበሩ ላይ በቡድን ተወያዩበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብላክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 39 መሰረት ለውጭ ጉዳይ ዘርፍ (ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት) ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

ለውጭ ጉዳይ ዘርፍ ሥልጣንና ተግባራት

- የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ሀገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በልሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤
- ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲጸድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግድታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

- የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣ የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድኦ የሚገኝበትን ሁኔታ ለሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ድጋፍ ይሠጣል፤ እንዲሁም በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የሀገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
- በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማህበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማህበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል። እንዲሁም የዲያስፖራ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤ በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
- ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ ሀገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤
- በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሀገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስላዎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል።

### 2.2.3 በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች

#### *2.2.3.1 የሥነ ምግባር ክፍሎችን ከማደራጀት አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሥነ ምግባር ክፍሎች በበቂ የሰው ኃይል፣ በጀትና ቁሳቁስ በአግባቡ ማደራጀት ለብልሹ አሰራርና ለሙስና ተጋላጭነትን በመቀነስ፣ ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት በማስፈን እና በማጎልበት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ነገር ግን የፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015) የተጠና የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር የሚገኙት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በቂ የሰው ኃይል፣ በጀትና ቁሳቁስ አለመደራጀታቸውን ለመረዳት ተችሏል። በተጨማሪም፣ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር ያሉ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በበቂ ቅንጅት አለመስራታቸው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ይህ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና ተጋላጭነታቸውን ከፍ እንደሚያደርግ ያመለክታል።

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች በቡድን (ከ3-7 ተሳታፊዎች) በመሆን በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በበቂ ሁኔታ በሰው ሃይል፣ በጀትና በቁሳቁስ በአግባቡ አለመደራጀታቸውና በቅንጅት አለመስራታቸው የሰራተኞችን የሥነምግባር ጉድለቶችን በመከታተልና የሥነምግባር ጥሰቶች እንዳይከሰቱ ቀድመው ከመከላከል እና ተከስተውም ሲገኙ አስፈላጊውን የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ከመውሰድ አኳያ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖና ለሙስና ተጋላጭነትን እንዴት እንደሚጨምር በዝርዝር በመወያየት ዋና ዋና ሃሳቦችን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

### *2.2.3.2 ተጠያቂነትንና ግልፅነት ከማስፈን አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

የተጠያቂነት ስርአት ማስፈን በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ያሉት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊቶቻቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበትና ተጠያቂ በመሆን የሙስና ስጋትንና ተጋላጭነትን እንዲቀንስና መልካም አስተዳደር እዲሰፍን ይረዳል። የተጠያቂነት ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ያሉ አመራርና ሰራተኞ በህግ ከተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት ውጪ እንዳይጠቀሙ በማድረግ የሙስና ስጋትና ተጋላጭነት ምጠን እንዲቀንስ ይረዳል።

ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል አንዱ የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና በአግባቡ መተግበር ነው። የሥነምግባር ደንብ አለመኖርና በአግባቡ አለመተግበር ዘርፍን ለሙስና ስጋትና ተጋላጭነቱን ከፍ የሚያደርገው መሆኑን መገመት ይቻላል። በተጨማሪም በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ከስነምግባርና ከተጠያቂነት ጉደለትና አኳያ ለሙስና ከፍተኛ ስጋትና ተጋላጭነትን ከሚጨምር ዲርጊቶች ውስጥ አንዱ ህገውጥ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት አጠቃቀም ነው።

**አስረጅ ናሙና**

አቶ አለማየሁ በኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ውስጥ የሚሰሩ ከፍተኛ ባለስልጣን ሲሆኑ በስራቸው ምክንያት የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ተሰጥቷቸዋል። ይህ ፓስፖርት አቶ አለማየሁ ቀላል እና ፈጣን ጉዞን እንዲኖራቸው አስችሎአቸዋል። ሆኖም፣ አቶ አለማየሁ ይህን ልዩ መብት በተሳሳተ መንገድ ተጠቅመው በዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ሽፋን በመንግስት ገንዘብ ወደ

ውጭ ሀገር ጉዞ ያደርጋሉ። በጉዞው ወቅትም ለራሱ እና ለቤተሰቡ ውድ ሽቀጣ ሸቀጦች፥ ለንግድ ውድ እና የተከለከሉ መጠጦችን በመግዛት ወደ ሀገር ቤት በማስገባት አትርፈው በመሸጥ ሃብት ያካብታሉ። በተጨማሪም ከሀገር ሲወጡም እድሉን በመጠቀም በግል ንግድ ተሰማርተው በውጭ ሀገር የንግድ ኮንትራቶች በመፈረም ለግል ጥቅማቸው ተጠቅመዋል። ውድ ሰልጣኞች በዚህ ምሳሌ ውስጥ አቶ አለማየሁ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርትን እንዴት ለግል ጥቅማቸውን እንደተጠቀመበት እና ድርጊቱ ለሙስና ስጋትናተጋላጭነትን እንዴት መፍጠር እንደሚችል በቡድን በመወያየት ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

በሌላ በኩል የግልፅነት ስርአት መስፈን ተቋማት ለዜጎቻቸውና ለህብረተሰቡ ለሚሰጡተት አገልገሎት የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮች መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር አንዱ ገጽታ ነው። በተጨማሪም ግልፅነት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖላሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭነታቸውን እንዲቀንሱ ይረዳቸዋል ።

ግልፅነት በተመለከተ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015) ጥናት እንደሚያመለከተው በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በበቂ ሁኔታ ተደራሽ የሚያደርጉበት አሰራር በቂ አለመሆኑ ያመላክታል። ይህ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የተመደበላቸውን ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን በተመለከተ ጥያቄ የሚያስነሳና ግልፅነት አለመኖሩ አንድ የሙስና ስጋት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዘጠኞች እና ሌሎች አካላት በበቂ ሁኔታ መረጃዎችን በመስጠት ተደራሽ አለመሆናቸውን የጥናት ውጤት አመላክቷል ። በተለይም ሚዲያ (የምርመራ ጋዜጠኝነት) ሙስናን ለህዝብ እይታ በማጋለጥ እንዲሁም ያለምንም ተጠያቂነት የሚፈፀሙ ጎጂ ስራዎችን በመዋጋት ረገድ ከሚጫወተው ወሳኝ ሚና አንፃር የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ አለመሆን የሙስና ስጋትና ተጋላጭነታቸውን ከፍ እንዲል ያደርገዋል ።

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የፀደቀ የሥነምግባር ደንብ አለመኖርና የፀደቀውም በአግባቡ አለመተግበሩ እንዲሁም ዘርፍ ለሚዲያ በተለይ ለምርመራ ጋዘጠኞች በበቂ ሁኔታ

መረጃዎችን በመስጠት በኩል ተደራሽ አለመሆኑ ከተጠያቂነትንና ግልፅነት ከማስፈንና ድርጊቱ ለሙስና ለብልሹ አሰራር እንዴት እንደሚያጋልጥ በቡድን (3-7) በመወያየት ሃሳባችሁን በዝርዝር ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

### *2.2.3.3 አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

**የማንቂያ /ሀሳብ ማፍለቅ ጥያቄዎች**

ውድ ሰልጣኞች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ መተግበር እንዴት ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን መቀነስ ያስችላል? ከሆነ እንዴት? ተወያዩበት

አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ መተግበር ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን በመዋጋት ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የህግ የበላይነት በማስፈን የተቋማትን የሙስና ስጋትና ተጋላጭነትን ትርጉም ባለው መልክ እንዲቀንሱ ይረዳቸዋል፡፡ ተቋማት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ መሻሻልም ይኖርባቸዋል፡፡ በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 ዓ.ም የተጠና የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በውጭ ጉዳይ ዘርፍ አዳዲስ ህጎችን የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ በበቂ ሁኔታ እየተሰሩ አለመሆናቸውን፣ ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ዙሪያ በቂ ስልጠና አለመሰጠቱ እንዲሁም ፀድቀው የሚወጡ ህጎችና መመሪያዎች ተደራሽ አለመደረጋቸው በአግባቡ አለመተግበሩ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ አመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጉዳዮች ላይ ስልጠና አለመሰጠቱ በሠራተኞች ሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ አስተዋጽኦ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ማነስ ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ክፈተት የሚፈጥር ስለሆነ ተቋማት ለሙስናና ለብልሹ አሠራር ተጋላጭነታቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡

### *2.2.3.4 የንብረት አስተዳደር ስርአትን ከመዘርጋት አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

በተቋማት ውስጥ የሚገኙትን ማናቸውም ንብረቶች በአግባቡ ማስተዳርናለተፈለገው ዓላማ ማዋል እንዲሁም ውጤታማ የንብረት አስተዳደር ስርአትን መዘርጋት ተቋማትን ውጤታማ ከማድረግ

ባሻገር በተቋሙ ውስጥ ብልሹ አሠራሮች እንዳይኖሩ ወይም እንዲቀንሱ በማድረግ ተቋማት ለሙስና ያላቸውን የተጋላጭነት ዕድል እንዲቀንስ በማድረግ ሂደት ውስጥ ሚናቸው የጎላ ነው፡፡ ንብረትን ከማስተዳደር አኳያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ውስጥ የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ያለአገልግሎት የተቀመጡትን (ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱትን) የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተከተለ መልኩ ማስወገድ ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከንብረት አስተዳደር አኳያ በ2015 ዓ.ም የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የቢን ካርድ እና የቋሚ ንብረት ምዝገባ አጠቃቀም ስርዓትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ወደተሟላ የአውቶሜሽን ስራ (IFMIS) ለማስገባት ጥረቶች መደረጋቸው ፣ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓትና ዓመታዊ የንብረት ቆጠራም ተግባራዊ መሆኑን ፣ ጊዜያቸው ያለፈባቸው (አገልግሎት የማይሰጡ) ኮሚፒውተሮች፣ ላፕቶፖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች እና የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች አስወጋጅ ኮሚቴ በማዋቀር ለተለያዩ ድርጅቶች በስጦታ መልክ በመስጠት እንዲወገዱ መደረጋቸውናየተከማቹ ጋዜጦችን በግልፅ ጨረታ እንዲወገዱ መደረጋቸው የጥናት ውጤት አሳይቷል ፡፡ ነገር ግን ከዘርፉ የተገኙ መረጃወችና የጥናት ውጤት እንደሚያመለክቱት በውጭ ጉዳይ ዘርፍ  በወቅቱ መወገድ የነበረባቸው የተለያዩ ንብረቶች ሳይወገዱ ቀርተው ለብክነት ተዳርገዋል፡፡ በተጨማሪም በ2013 ዓ.ም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 15 ተሽከርካሪዎች ተበላሽተው ከአገልግሎት ውጭ ስለመሆናቸው ግንቦት 18፣ 2013 በኮሚቴ ተጣርቶ ንብረቶቹ እንዲወገዱ በበላይ አመራሮች ግንቦት 27፣ 2013 የተወሰነ ቢሆንም የተቋሙ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት ለተቋሙ የበላይ ሀላፊዎች በግንቦት 17፤ 2014 በፃፈው ምክረ ሀሳብ ንብረቶቹ እንዳልተወገዱ አረጋግጧል፡፡  ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ ለሙስናና ለብልሹ አሠራር የሚያጋልጡ የንብረት አስተዳደር ተግባርና ስርአት መኖሩንና ተቋሙ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት ከፍ ያደርገዋል፡፡

#### *2.2.3.5 የግዥ አስተዳደር ስርአትን ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሚሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የዕቃና የአገልግሎት

ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሚሟላት የንመንግስት የግዥ ስርአትን መከተል ያስፈልጋል። በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት ከስራ ክፍሎች በሚሰበሰብ የግዥ ፍላጎት መሰረት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ እንደሚያዘጋጁ፣ በመቀጠልም በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተገምግሞ እና ፀድቆ ወደ ግዥ ኤጀንሲ እንደሚላክ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 ከተጠና የጥናት ውጤት ለማወቅ ተችሏል።

ነገር ግን ከተጠናው ጥናት ለመረዳት እንደተቻለው በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት እና በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት በ2014 በጀት ዓመት ከተከናወኑ ግዥዎች መካከል በድምሩ 6.7 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ እንዲሁም ከ12.2 ሚሊዮን ብር በላይ በውስን ጨረታ የግዥ ስርአት ተከናውነዋል። በተመሳሳይ ዓመት በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ከ2.8 ሚሊዮን ብር በላይ ከዕቅድ ውጭ ግዥ ተከናውኗል። በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከ 6.4 ሚሊዮን ብር በላይ የቀጥታ የግዥ ዘዴን በመጠቀም የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች ግዥ መፈፀሙን በ2013 የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ላይ ተገልጿል።

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች፣ በቡድን በመሆን (3-7) ከዚህ በታች ባሉት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ሃሳባችሁን ለተሳታፊዎች አቅርቡ ።

- በሚሊዮን ብር የሚቆጠሩ ከዕቅድ ውጭ፣ በቀጥታ፣ በውስን ጨረታ እና በፕሮፎርማ የተከናወኑ ግዥዎች መኖራቸው ምን ያህል ሙስናን ያበረታታል?
- የግዥ ሂደቱ ሚዛናዊ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ ለብክነት እና ለሙስና እንዴት ያጋልጣል? ከእነዚህ ችግሮች ጋር በተያያዘ ምን ዓይነት የመንግስት ሃብት ብክነት ሊከሰት ይችላል?
- የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የግዥ ስርዓት ለሙስና እንዴት እንደሚያጋልጥ በዝርዝር አብራሩ።

### *2.2.3.6 የሰው ሃብትን በአግባቡ ከማስተዳደር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

**የማንቂያ /ሀሳብ ማፍለቅ ጥያቄዎች**

ውድ ሰልጣኞች በእናንተ አስተሳሰብ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሰራተኞ ቅጥርና ምደባ ምንን መሰረት ያደረገ ነው? ከልምዳችሁ በመነሳት የሰራተኞች ቅጥርና ምደባ በብሔር፣በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከትና በተለያዩ ጥቅማ ጥቅምን መሰረት አድርጎ ሲከናወን አጋጥሟችሁ

ያውቃል?  ካጋጠማችሁ ችግሩን ለመቅረፍ ምን አደረጋችሁ? ተቋማችሁ ላይ ያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖስ ምን ይመስላል?

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ግብዓቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው የሰው ሃብት ነው:: የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስኬትም የሚረጋገጠው የተቋሙን የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር የሚያስችል አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ሲቻል ነው:: በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር እና ሌሎች ኮሚቴዎች ማደራጀታቸው እና የሰራተኛ ቅጥር ለመፈፀም ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሃን የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን፣ የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ መሆኑን በ2015 የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጥናት ውጤት አሳይቷል::

ነገር ግን ከነበረው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት በመንግስት በኩል ከ2012 ዓ.ም በፊት ሃሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ እንዲከናወን አቅጣጫ ቢቀመጥም በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከተከናወነው ጅምር ስራ ውጪ በቀሪዎቹ ሁለቱ ተቋማት የሃሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ እየተሰራ አለመሆኑ መረዳት ተችሏል:: ይህ ደግሞ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ያሉትን ሰራተኞች የትምህርት ዝግጅታቸውንና የስራ ልምዳቸውን መሰረት አድርገው በተገቢው የስራ መደብ ላይ ተመድበው ስራቸውን በብቃትና በትጋት እንዳይሰሩ እና ለተለያዩ የሙስና አደጋዎች እንዲጋለጡ እድል የሚፈጥር ነው::

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች፣ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ ሲታይ የነበረው ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ በአግባቡ አለመተግበሩ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርአት አለመገንባት ተቋማቱን ለከፍተኛ የሙስና አደጋ እንዴት እንደሚያጋልጣቸውና የሰነድ ማጭበርበር ድርጊትም በሕገ-ወጥ መንገድ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሆን ተብሎ የሚደረግ አታላይ ድርጊት ሲሆን በተቋማቱ በቂ የማጣራት ስርአት ባለመኖሩ ሰዎች በሀሰተኛ ሰነዶች ጥቅም እንዲያገኙ ማስቻሉ እንዴት ከሙስና ጋር እንደሚያያዝ በቡድን በመወያየት ለተሳታፊዎች ያቅርቡ::

### *2.2.3.7 የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓትን ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። የሃብት ምዝገባ በተመለከተ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት በርካታ አመራሮችና ሰራተኞች ሀብታቸውን ያስመዘገቡ ቢሆንም አብዛኞቹ ሰራተኞች እንዳላስመዘገቡ በ2015 የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ካደረገው የዳሰሳ የጥናት ውጤት መገንዘብ ተችሏል። ሰራተኞች ሀብታቸውን ወቅቱን ጠብቀው አለማስመዝገባቸው የጥቅም ግጭቶች እንዲፈጠሩ እና ምንጫቸው ያልታወቀ የሀብቶች ክምችት እንዲኖር ስለሚያደርግ እንደ አንድ የሙስና ስጋት ምንጭ ይወሰዳል።

**አስረጅ ናሙና**

በውጭ ጉዳይ ዘርፍ በ2015 በተደረገ የዳሰሳ ጥናት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የሃብት ምዝገባ ማድረግ የሚገባቸው አመራሮችና ሰራተኞች በሙሉ በህጉ መሰረት ሀብታቸውን አስመዝገበዋል። ነገር ግን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካሉት ከ1400 በላይ አመራርና ሰራተኞች ውስጥ ሀብታቸውን ያስመዘገቡት 171 ብቻ መሆናቸውን የጥናት ውጤጡ አሳይቷል።

### *2.2.3.8 የፕሮጀክቶች አስተዳደር ሥርዓትን ከመተግበር አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜያቸው ድረስ አግባብነት ባላቸውን ህጎችና መስፈርቶችን ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ውጤታማ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት ሊኖራችው ይገባል ። ነገር ግን በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የነበሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ውጤታማ የፕሮጀክቶች አስተዳደር ሥርዓት ባለመኖሩና የተለየ የኦዲት መዋቅር ካለመኖሩ የተነሳ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ለሃብት ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ 2015 የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ውጤት አሳይቷል። በተለይም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ማጠናቀቅ አለመቻሉን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ፕሮጀክቶች በተመለከተ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለያዩ ሀገራት እያስገነባቸው ከሚገኙ 11 የኤምባሲዎች ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ ሲሆኑ

ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸውና ተቋራጩ ክስ የመሰረተበት እንዳሉም የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 ካደረገው የዳሰሳ የጥናት ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 የተደረገው የዳሰሳ ጥናት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ያሉትን ችግሮች የሚያሳዩ አራት አሳሳቢ አስረጂ ናሙናዎችን እንደሚከተለው አውጥቷል፡፡

- በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች (ለምሳሌ 4.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚገመት የዋሽንግተን የጽ/ቤት፣ የአምባሳደር መኖሪያ ቤት እና የቀድሞ ጽ/ቤት ህንፃ ሙሉ ዕድሳት ስራ ፕሮጄክት በ2013 በጀት ዓመት ላይ የመጨረሻ ደረጃ ርክክብ መደረግ የነበረበት በተለያዩ ምክንያቶች በወቅቱ ርክክብ ሳይደረግ ቀርቷል) ፡፡ የፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ ከፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ጉድለት ማሳያና አሳሳቢ የሙስና ስጋት ነው፡፡
- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው (ሶስት ፕሮጀክቶች፥ የለንደን ፕሮጀክት 434 ሺህ በላይ የእንግላዝ ፓውንድ፣ የቻይና ፕሮጀክት 5.3 ሚሊዮን በላይ የቻይና የን እንዲሁም የጅቡቲ ፕሮጀክት 46 ሚሊዮን በላይ የጅቡቲ ፍራንክ) ፡፡ ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበት አሰራር (Variation work order) ቀድሞ የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ከመገምገም እና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ጠቋሚና እንደ አንድ የሙስና ስጋት ሊቆጠር ይችላል፡፡
- ተቋራጩ ክስ የመሰረተበት (የቱርክ ፕሮጀክት 16.4 ሚሊዮን የቱርክ ሊሬ)፣
- የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት national democratic institute (NDI) ከሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ጥናት ለማድረግና የተቋሙን አቅም ለመገንባት ጀምሮ የነበረው ፕሮጀክት በወቅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን በኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክት አሰራርን በተመለከተ የሂሳብ ክፍያ አፈፃፀም እና የፕሮጀክት ስራ አሰራር ግልፅነት ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ እንደ ሙስና ስጋት ሊወሰድ ይችላል፡፡

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች በቡድን (የቡድን አባላት እንደየተሳታፊው ብዛት ከ3-7 ሊሆኑ ይችላሉ) በመወያየት ከተጠቀቀሱት ናሙናዎች በመነሳት ዋና ዋና ክፍተቶችን በመለየት የችግሩ ምንጭን መፍትሄ የምትሉትን በዝርዝር አስቀምጡ ፡፡

### *2.2.3.9 የኦዲትና ቁጥጥር ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና የሙስና ስጋቶች*

ጠንካራ የኦዲትና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችና ሙስናን በእጅጉ እንዲቀንሱ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም ተቋማት ህጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ በየጊዜው በውስጥም ሆነ በውጭ ኦዲተር የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሠራራቸውን የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሠረት በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ሥር የሚገኙ ተቋማት በየሩብ ዓመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ የሰሩና አብዛኞቹ የተቋማት አመራሮች የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የማካሄድ ልምድ ያላቸው ቢሆንም የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች መሰረት አድርገው የተደረጉ ማሻሻዎችን በተመለከተ ግን የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ማሻሻያዎችን ማድረጉን በ2015 በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጥናት ውጤት ያመላከተ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ሁለት ተቋማት ግን ማሻሻዎችን ስለማድረጋቸው የጥናቱ ውጤቱ አላመላከተም፡፡ በተጨማሪም የሒሳብ አያያዝ ሥርዓትን ማሻሻልን በተመለከተ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS - Integrated Financial Management Information System) እየተተገበሩ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤቱ አያሳይም፡፡ ይህ ደግሞ ጠንካራና ውጤታማ የፋይናንስ ቁጥጥር ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ ተቋማት ለሙስናና ለብልሹ አሰራሮች እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል፡፡

**አስረጅ ናሙና**

እንደምሳሌ በ2014 በጀት ዓመት ከተካሄዱ የውጭና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች ግኝት የተለዩ የአሠራር ክፍተቶች ውስጥ፡-

ዋና ኦዲተር በ2014 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ባደረገው ኦዲት የአገልግሎት ብቸኛ አቅራቢ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ከብር ሁለት ሚሊዩን በላይ በቀጥታ ግዥ መፈጸሙና በመንግስት ግዥ መመሪያ ለውስን ጨረታ ከተፈቀደው የብር መጠን በላይ በድምሩ ብር 3.89 ሚሊዮን ብር በላይ ግዥ ተፈፀሟል፡፡ በተጨማሪም የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት ላይ በወጪ መመዝገብ የሚገባው ከብር 1.14 ሚሊዩን በላይ በገቢ የተያዘበት እና በሂሳብ መደብ ተለይተው

ከብር 2.6 ሚሊዩን ብር በላይ ያልተመዘገበበት ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም ግዥ የተፈፀመባቸው ንብረቶች ገቢ ስለመደረጋቸው ማረጋገጫ ሳይቀርብ ብር 274,206.07 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ ከብር 54.9 ሚሊዮን በላይ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ አለመወራረዱ የታዩት የአሠራር ክፍተቶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በ2014 በጀት ዓመት የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ባካሄደው የውስጥ ኦዲት ስልጠና ባልተሰጠበት ሁኔታ ለስልጠና ማዕከል ብር 148,404 በወጪ ሂሳብ መመዝገቡንና አገልግሎት ከሰጠ ድርጅት መቀነስ የሚገባው ሁለት በመቶ ታክስ ብር 83,060.87 ሳይቀነስ ክፍያ መፈፀሙንና ከሐምሌ 2013 እስከ ሰኔ 2014 ዓ.ም. ድረስ ወጪ ተደርገው በድምሩ ብር 5,652,316.07 ሳይወራረድ የቀረ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

**የፌደራል ዋና ኦዲተር የ2009 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኦዲት ግኝት በተመለከተ** የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በ2009 ዓም 331 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ከተፈቀደለት በጀት ርዕስ ውጭ የገንዘብ ሚኒስቴርን ፍቃድ ሳያገኝ በጀት አዛውሮ መጠቀሙ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ሚኒስቴሩ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከመጠቀሙ በፊት የገንዘብ ሚኒስቴርን ፈቃድ ማግኘት የነበረበት ሲሆን ይህን ሳያደረግ መቅረቱ መንግሥት ያጸደቀውን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መጣሱንና ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የመጋለጥ እድሉ ከፍ ያለ እንደነበር አመላካች ነው፡፡

በተጨማሪም ለሰንዓ ፎረም ተብሎ ከ27 ሚሊዮን ብር በላይ በሚመለከታቸው የሚኒስቴሩ የሥራ ኃላፊዎች ጸድቆ እንዲወጣ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ መፈጸሙን በኦዲት ምርመራ ተጋልጧል፡፡

ሚኒስቴሩ በካንቤራ፣ በብራስልስና በዋሽንግተን ውል ሳይታሰር እንዲሁም ከመንግስት የግዢ አዋጅ ውጭ ያለ ውድድር ከአንድ አቅራቢ የአምስት ሚሊዮን 953 ሺህ ብር የተለያዩ ግዢዎች መፈጸማቸውን ምርመራው አረጋግጧል፡፡ የፌደራል መንግስት የግዢ ስርዓትን በጣሰ መልኩ አንድ ሚሊዮን 894 ሺህ ብር የተለያዩ የአገልግሎት ግዢዎች መፈፅማቸው እንደ ትልቅ የሙስና ስጋት ሊወሰድ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ለሙስና ስጋት የሆኑ አሰራሮችና ሂደቶች (processes) እንዳሉትና የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

**አስረጅ ናሙና**

ከውል ጋር የተያያዘ ክፍተት፡-በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኢምባሲ ያከራየውን ህንፃ ከተከራዩ አካል ጋር ሳገናኘው ደላላ ለሰጠው አገልግሎት አንዴ ከፍሎ መለያየት ሲቻል በየጊዜው ገደብ በሌለው ተጠቃሚ የመሆን መብት በውሉ ተካቶ በመገኘቱ ያለአግባብ ኢምባሲው ወጪ እንዲያወጣ

ተደርጓል (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት፤ መጋቢት፤2014) ።

በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ ዋና ዋና አሰራሮችና ደረጃቸውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ. | የተለዩ አሰራሮች | ለመለየት የተቀመጡ መስፈርቶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከኦዲት ሪፖርት (45%) | ከኢንስፔክሽን ሪፖርት (30%) | በሀላፊዎች የተሰጠ መረጃ (25%) | ድምር 100 | ደረጃ |
| 1 | የተሽከርካሪ አስተዳደርና አጠቃቀም (ጥገና፣ ስምሪት፣ መለዋወጫ አወጋገድ) | 30 | 25 | 25 | 80 | 1ኛ |
| 2 | የተሽከርካሪ ነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር | 36 | 25 | 17.5 | 78.5 | 2ኛ |
| 3 | የፕሮጀክት አፈፃፀም (በሀገር ውስጥና በኢምባሲዎቻችን የሚገነቡ/የሚጠገኑ ህንፃዎችን ያካትታል) | * | 25 | 17.5 | 77.3 | 3ኛ |
| 4 | የግዢ አፈፃፀም/ሂደት | 30 | * | 20 | 71.4 | 4ኛ |
| 5 | የስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ፋክስ እና ኢ-ቪዲዎ አጠቃቀም | * | 25 | 12.5 | 68.2 | 5ኛ |
| 6 | የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም | 22.5 | * | 10 | 46.4 | 6ኛ |

ምንጭ፦የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት በ 2014 የተጠና

## 2.3 ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

### 2.3.1 መግቢያ

በዚህ ክፍል በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚከሰት ሙስና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶችን ይመለከታል። የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ሙስና የሀገርን ገፅታ በማበላሸት እንዴት ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ እና ተሰሚነት እንደ ሚቀንስ ያቀርባል። ቀጣይ ክፍል ሙስና እንዴት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች እና የልማት ትብብሮችን ሊያሸሽ እንደሚችል ያሳያል። ሶስተኛው ንዑስ ክፍል በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ዳያስፖራው የሚገባቸውን እርዳታ ከኢትዮጵያ ሚሲዮኖች እንዳያገኙና መብታቸው ተገቢውን ክብር እንዳያገኙ ሙስና እንዴት አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይቀርብበታል። ቀጣይ ንዑስ ክፍል ሙስና ሊያስከትላቸው የሚችለው የውጭ ዕዳን በመጨመር እና የፋይናንስ ያላመረጋጋት በማምጣት እንዴት ሉዓላዊ የፖሊሲ ነጻነትን እንድሚጎዳ ያሳያል። ንዑስ ክፍል አምስት ሙስና ሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች እንዲስፋፉ እንዴት መንገድ እንደሚከፍት እና ብሄራዊ ደህንነታችንና ጥቅሞቻችን ለአደጋ እንዲጋለጡ እንደሚያደርግ ያሳያል።

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚፈጸሙ የሙስና ተግባራት ምን ዓይነት ጉዳቶችን ያስከትላሉ? የምታውቁትንና ያጋጠማችሁን የሙስና ወንጀል ጉዳቶች ዘርዝሩ
2. በዚህ ዘርፍ የሚፈጸም ሙስና ከሌላው ዘርፍ ሙስና እንዴት ይለያል? ለብሄራዊ ደህንነትና ሀገራዊ ህልውና ያላቸው አንድምታ ምንድን ነው?

### 2.3.2 የሀገር ገጽታ ጉዳቶች

የጥንታዊ ስልጣኔ እና የአድዋ ድል ባለቤት እና የአፍሪካ ዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችው ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ በሷ አቅም ደረጃ ካሉ ሀገራት እጅግ በጣም የተሻለ እውቅናና ተፅዕኖ ያላት ሀገር ናት። ዘላቂነት ያለው ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገር ሆና እንድትቀጥል ደግሞ የውጭ ጉዳይ ዘርፉ ቀዳሚና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል። ካለብን ሀገራዊ ኃላፊነት፣ አካባቢያዊ የጂኦፖለቲካ ተጽዕኖ እና የሀብት ውስንነት አንጻር፣ የውጭ ጉዳይ ሴክተሩ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ገፅታ እና ተፅዕኖ

የመገንባት እና የመጠበቅ ስኬት ከፍተኛ እምርታ ያለው ነው፡፡ ዘርፉ የኢትዮጰያን ብሄራዊ ጥቅምና መልካም ስም በአለም አቀፍ መድረክ ከማስከበር አንጻር ጉልህ ሚናዎችን ሲጫወት ኖሯል፡፡ ለአብነት ያህል እንደ እነ አክሊሉ ሀብተወልድና ከተማ ይፍሩ ያሉ በትምህርትም በዲፕሎማሲም ከፍተኛ ልምድ የነበራቸው የኢትዮጵያን ስም በዓለም መድረክ ከፍ ያደረጉ የውጭ ጉዳይ ሀላፊዎችና ዲፕሎማቶች ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ዘርፉ ይህንን መልካም ስም ይዞና የሀገራችንን የቀጠናው የመሪነት ሚና በቀጣይነት እንዲያረጋግጥ፣ የሙስና ስጋቶችን በቅድሚያ እና በጥንቃቄ መርምሮ በማያሻማ እና የዘርፉን መልካም ስም በማይነካ መልኩ መከላከል ያስፈልጋል፡፡ከዚህ አንጻር መሰረታዊው ጉዳይ የፕሮፌሽናል ባለሙያ ምልመላ፣ ቅጥር፣ እድገት እና ስምሪት ነው፡፡ የዉጭ ጉዳይ ዘርፍን ለማቋቋምና ለማስተዳደር የወጡ አዋጆችና መመሪያወች በግልጽ እንዳስቀመጡት የዲፕሎማቲክ ሰራተኞች ምልመላ ዕውቀትና ችሎታን መሰረት ባደረገ ግልጽ ውድድር እንደሚፈጸም ተደንግጓል፡፡ ጥሩ ዲፕሎማት የሀገሩን ጥቅምና ፍላጎት በውል የተረዳ፤ የሀገሩን እውነታና ፖሊሲ ማስረዳትና ማሳመን የሚችል፤ በውጭ ሀገራት ያሉ እንቅስቃሴዎችና አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ አዝማሚያዎችን ቀድሞ በመገንዘብና በመተንተን ሀገሩ አስፍላጊ ጥንቃቄና እርምጃ እንድትወስድ መረጃ በወቅቱ ማድረስ ከብዙ በጥቂቱ ዋነኛ ተግባሩ ነው፡፡ ዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችና ካሪር ዲፕሎማቶች ባለቤት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አልፎ አልፎ ግን የዘርፉንና የብሄራዊ ገጽታን የሚያጠለሹ የሰው ኃብት ምደባና ሌሎች ብልሹ አሰራሮች እየተስተዋሉበት እንደሆነ መረጃወች ይጠቁማሉ፡፡

ባለፉት አስርተ ዓመታት በአብዛኛው የተለመደው የአምባሳደሮች ሹመት፣ በ2016 ከተደረገው በርከት ያሉ የወጣት ከሪር ድፕሎማቶች ምደባ በስተቀር፣ የፖለቲካ ታማኝነትን መሰረት ያደረገ እንደሆነና እነዚህ ተሿሚዎች በመስኩ ቀጥተኛ የትምህርት ዝግጅት ወይም ልምድ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከተመለመሉ በኂላ የሚሰጥ አጭር የዲፕሎማቲክ ስልጠና ብቁ ዲፕሎማት ያደርጋቸዋል ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ልምድና በቂ ዝግጅት የሌላቸው ዲፕሎማቶች የሀገርን ጥቅምና መልካም ስም በአለም አቀፍ መድረክ ማስከበር አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የሀገርን ብሄራዊ ጥቅም ሊጎዳ፤ መልካም ስሟን ልያጠለሽ፤ ይባስ ብሎም  የሀገርን ሚስጥር ለጠላት እንዲተላለፍ መንገድ ሊከፍት ይችላሉ፡፡

የፖለቲካ ታማኝነት እንደመስፈርት ማገልገል ካለበት እንኳ ተሿሚዎች በሙያው የሰለጠኑና በቂ ልምድ ያላቸው መሆን አለባቸው።

**የቡድን ውይይት**

3. የዲፕሎማት ምደባ ሙያንና ስልጠናን ከማድረግ ይልቅ በቅርበት፣ በዘመድ አዝማድ ወይም በፖለቲካ ታማኝነት (የጡረታ ስጦታ) ማድረግ በአለም አቀፍ መድረክ ሀገሪቱ ጥቅሞቿን እና ተሰሚነቷን ከማስከበር አንጻር የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ምንድን ነው?
4. የውጭ ጉዳይ ዘርፉ የተወሰና የማህበረሰብ ክፍል በተውጣጡ ባለሙያተኞች ቁጥጥር ስር ከገባ በብሄራዊ ገጽታ ላይ ምን ዓይነት ጉዳት አለው? የማህበረሰብ ውክልና ለማሻሻል ተብሎ የዘርፉ ሰው ኃብት እንደገና ቢደራጅስ ምን ጥቅሞች እና ጉዳቶች ይኖሩታል?
5. በዘመቻ መልክ በርካታ ወጣት ድፕሎማቶችን በአንድ ጊዜ በአምባሳደርነት መሰየምስ ምን ዓይነት በጎ እና በጎ ያልሆኑ ተጽዕኖዎችን ይፈጥራል?

### 2.3.3 የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እና የልማት ትብብር ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች

ኢትዮጵያ የምታልመውን ፈጣን እድገትና መልማት በአጭር ጊዜ ለማሳካት ሀገሪቱ ትኩረት ሰጥታ እየሰራችበት ባለው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አንፃር የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን መሳብ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድኦ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ግንባር ቀደም ሚና ይጠበቅበታል። ይሁንና በዘርፉ የሚመደቡ ዲፕሎማቶች ብቃትን መሰረት ካላደረጉ እና ምግባረ ብልሹ ከሆኑ ከውጭ ኢንቨስተሮች፣ የተራድዖ ድርጅቶች፣ ቱሪስቶች ወዘተ ግለሰቦቹ ስለሚያገኙት ጥቅም እንጂ ስለሀገሪቱ ጥቅሞች አያሳስባቸውም።

በዚህ ምክኒያት ሀገርን ሊጠቅሙ የሚችሉ ኢንቨስተሮች፣ የልማትና ተራድዖ ድርጅቶች፣ ቱሪስቶችና ሌሎችም ሳይመጡ ይቀራሉ። በተቃራኒው አቅምም ብቃትም የሌላቸው የውጭ ዜጎች ከውጭ ጉዳይ ዘርፍ ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር በኢንቨስተር ስም በመግባት ውስን የሆነውን የሀገሪቱን ሀብትና ሰፋፊ መሬት በነፃ እንዲያገኙ ከተደረገ እና የባንክ ብድር ከተመቻቸላቸው በኋላ ይህ ነው የሚባል ልማት ሳያለሙ መሬቱን በመሸጥ ከፍተኛ ሀብት ወደ ውጭ እንዲወጣ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህ ድርጊት ሀገሪቱን ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍላት ይችላል።

ለሰብአዊም ይሁን ለልማት የሚመጣ የውጪ ዕርዳታ ለታለመለት ግብ ካልዋለ ወይም ከተመዘበረ ዕርዳታ ሰጪ ሀገራት ወይም ተቋማት የሚሰጡትን ድጋፍ ሊያቋርጡ ወይም ሊቀንሱ ይችላሉ። በዚህም ምክኒያት አስቸኳይ ድጋፍ የሚፈልጉ ዜጎች ችግር ላይ ይወድቃሉ፤ የውጭ ኢንቨስተሮች ኢንቨስት ለማድራግ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከውጭ ሚሲዮኖች ጀምሮ ወደ ሀገር ከገቡም በኋላ በተለያዩ አካላት የሚጠየቁት የእጅ መንሻ ወይም ጉቦ እንዲማረሩ ያደርጋቸዋል፡ ይባስ ብሎም ኢንቨስትመንቱን ወደ ሌላ ሀገር ሊያዞሩ ይችላሉ። በሙሰኛ ባለ ስልጣናትና ዲፕሎማቶች አሻጥር በህገወጥ መንገድ የሀገር ሀብት እና ገንዘብ ከሀገር እንዲሸሽ ሊደረግ ይችላል።

ከሚከተለው ማሳያ እንደምንመለከተው አንዳንድ ጊዜ በሌላ ሀገር ዲፕሎማቶች እና ባለ ስልጣናትም የሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም ይሚጎዱ እና የወዳጅ ሀገርን ፖሊሲ ያለአግባብ የሚቀይሩ የሙስና ተግባራትም በአንክሮ መከታተል እና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

**አስረጅ ናሙና**

*የአሜሪካ የሴኔት አባል እና የዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት ቦብ ሜንዴዝ ከ2018 እስከ 2022 ባሉት ዓመታት በስውር ከግብፅ ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት በማድረግ በአሜሪካ ምክርቤት ባላቸው የሴኔት የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ ሰብሳቢ(ቼር) ሀላፊነትን በመጠቀም የግብፅ መንግስትን ፍላጎት ሲያራምድ ቆይቷል። ለምሳሌ በሰብአዊ መብት ጥሰት ምክኒያት የተቋረጠ በመቶ ሚሊየኖች ዶላር የሚቆጠር የአሜሪካ እርዳታ ለግብፅ እንዲለቀቅ ግፊት ማድርግ፤ በሚሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር ወታደራዊ እርዳታና ግዥ ከአሜሪካ በፍጥነት እንድታገኝ መርዳት( Bob Menendez's efforts to speed $99m in helicopter/tank ammunition to Egypt) ይገኙበታል። በተጨማሪም በማርች 2020 ሜንዴዝ ከግብፅ ባለስልጣናት ጋር በመገናኘት አሜሪካ በኢትዮጵያ ግድብ ዙሪያ በድርድሩ እንድትሳተፍ አንዲረዳ ተወያይተዋል። በኤፕሪል 2020 ሴናተሩ ለወቅቱ የአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስቴር ሀላፊ እና ለውጭ ጉዳይ ሀላፊ ግድቡን በተመለከተ በ3ቱ ሀገራት ሲካሄድ የነበረው ድርድር መስተጓጎል እንዳሳሰበው ገልጦ የውጭ ጉዳይ ቢሮ በጉዳዩ ዙሪያ በከፍተኛ ትኩርት በድርድሩ ሂደት እንዲሳተፍ በደብዳቤ አሳሰቧል። ከሰባት ወር በኋላ በወቅቱ የነበረው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ግብፅ ግድቡን ልታወድም ትችላለች አለ፤ አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ማድርግ ቀጠለች፤ የሚሰጡ በሚሊዮን የሚቆጠር እርዳታ አቋረጠች፤ ከትግራይ ጦርነት ጋር ተያይዞ (የሰባዊ መብት ጥሰት እንደሰበብ በመጠቀም ) እቀባዎችና ጫናዎች ተባብሰው ቀጠሉ። ከደርዘን በላይ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ኢትዮጵያን በተመለከተ ተሰብስቧል። ከዚህ ሁሉ ጫና በስተጀርባ በአብዛኛው ሜንዴዝ በፊት አውራሪነት ነበረበት። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሴናተሩ መንግስታዊ ሀላፊነትነ ለግላዊና ቤተሰባዊ ጥቅም ብሎም የግብፅን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ፍላጎት ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በህገወጥ መንገድ ከግብፅ መንግስት ተቀብሏል።በተከሰሱበት 16 አይነት የሙስና*

*ክስ በሁሉም ጥፋተኛነታቸው ተረጋግጧል። በተለይ የገንዘብ፣ የወርቅ (13 gold bars worth nearly $150,000 along with $500,000 in cash found in his New Jersey home during a 2022 raid by the FBI) እና ቅንጡ የመኪና ስጦታ ከሶስት የኒው ጀርሲ ነጋዴዎች(ቢዝነስሜን) ጉቦ በመቀበላቸው እንዲሁም ለግብፅ የውጭ ኤጀንት (acting as an overseas agent for Egypt) በመሆን ማገልገል ይገኝበታል።*

1. *በመጨረሻም ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም የመንግስትና የህዝብን አደራ በመዘንጋት ወዳጆቹን እና ሚስቱን ጭምር ለመጥቀም፣ ከግብፅ የደህንነት ሀላፊዎች ጋር በመገናኘት እንዲሁም ግብፅ በሚሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር ወታደራዊ እርዳታ ከአሜሪካ እንድታገኝ በመርዳት ከፍተኛ የህግ ጥሰትና የሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ለወራት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቶ ሀምሌ 2024 በተከሰሰበት ሁሉም ጉዳዮች ጥፋተኛነቱ ተረጋግጧል[1]።*

**የውይይት ጥያቄ**

2. ከላይ ከተጠቀሰው አስረጅ ናሙና  አንጻር የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እና መንግስት ምን ማድረግ ነበረባቸው(አለባቸው)?
3. ይህ ክስተት በኢትዮጵያ ላይ ምን ጉዳት ወይም ተጽዕኖ አደረሰ?

#### 2.3.4 በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራው) ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተጽዕኖዎች

አዲሱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል።ዳያስፖራው በእውቀት፣ በገንዘብ እንዲሁም በሚኖሩባቸው ሀገሮች የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ልምድ ተቋዳሽ በመሆናቸው ለትውልድ አገራቸው በእነዚህ ነገሮች ረገድ ሊሰጡት የሚችሉት ፋይዳም በተሻሻለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተገልጿል (አዲሱ የውጭ ጉዳይ ፓሊሲ ረቂቅ ሰነድ) ። ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ዕርዳታቸውን ሲሰጡ ነበሩ፤ አሁንም አሉ። በየዓመቱ

---

[1] Lauren del Valle, Kara Scannell, Sabrina Souza, Nicki Brown and Gregory Krieg, (July 2024) https://edition.cnn.com/2024/07/16/politics/bob-menendez-verdict/index.html

ከእነሱ ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ገንዘብም (ሬሚታንስ) በየጊዜው እያደገ የመጣ ሲሆን፣ ቀላል በማይባል ደረጃ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚደግፍ ነው። በእውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግርም ኢትዮጵያ ከእነሱ ብዙ ትጠብቃለች።

በሌላ መልኩ ደግሞ ከነሱ ጥቅምን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብትና ክብር ማስጠበቅ አስፈላጊ እና ተቀዳሚ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ሀላፊነትና ተግባር ነው። ዜጎች ህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከሀገር ሊወጡ ይችላሉ። በየትኛውም መንገድ ይውጡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከተው የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከዓለምአቀፍ ድርጅቶች እና አስፈላጊም ሲሆን ከሌሎች የአገር ውስጥ ተቋማት ጋር በመተባበር አደጋ ውስጥ ያሉ ዜጎችን ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስበትን መንገድ የማመቻቸት ሀላፊነት አለበት።

ይሁንና በአንዳንድ የውጭ ሀገር ሚሲዮኖቻችን ችግር ላይ የወደቁ ዜጎቻችንን የመታደግ ውስንነቶች እንዳሉ ይስተዋላል። በተለይ በርካታ ዜጎቻችን በሚገኙበት በመካከለኛው ምስራቅ ችግሮች ጎልተው ይታያሉ። ዜጎች አደጋ ላይ ወድቀው አስቸኳይ የቆንስላ ድጋፍና ክትትል በሚያስፈልጋቸው ጊዜ አገልግሎት እንደማያገኙ ከሚሰሙ የሚዲያ ሮሮዎች መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም በአረብ ሀገራት የሚኖሩ ዜጎች የኢምባሲ አገልግሎት ሲፈልጉ፤ ለምሳሌ የፓስፖርት እድሳት ሲፈልጉ ለማስፈፀም በአንዳንድ ሰራተኞች ከፍተኛ መጠን ያለው ጉቦ እንደሚጠየቁ ይነገራል።

ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ በዲያስፖራውና በመንግስት መካከል ጤናማ ግንኙነት ከሌለ የዲያስፖራው ተጽዕኖ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። በተለይ በርካታ ተጽዕኖ ፈጣሪ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው ሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ ሀገራት በተለያየ ጊዜ በሚደረጉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችና ሰልፎች የሚኖሩባቸው ሀገራት በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ፤ የዲፕሎማሲና የደህንነት ጫና ሊፈጥሩ ይችላሉ። በተለይ አሜሪካ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች በተደጋጋሚ በሚያደርጓቸው የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች የአሜሪካ መንግስት በሰብዐዊ መብት ጥሰት ሰበብ አንዳንድ ማእቀቦችን ሲጥልና ሰብዐዊ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፎችን ሲያቋርጥ ይስተዋላል። ከዚህም ባለፈ ዲያስፖራው አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በተቃውሞ ስም ከሌሎች በተለይ ከኢትዮጵያ ጋር ጥሩ ግንኙነት ከሌላቸው ሀገራት ጋር አብረው በመስራት የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት በሚጎዳ መልኩ ሲንቀሳቀሱ ይታያል።

ስለሆነም የውጭ ጉዳይ ዘርፉ በተለይ ኢንባሲዎቻችንና ሚሲዮኖቻችን ከዲያስፖራው ጋር ተቀራርበው በሀገር ጥቅም ጉዳይ በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ዲያስፖራው የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ በህብረት ሲንቀሳቀስ ውጤታም ስራ እንደሚሰራና በሀገርና በመንግስት ላይ ሊያሳድር የሚችልውን ያልተገባ ጽዕኖ መከላከል እንደሚቻል በቅርቡ የኢትዮጵያውያን ዲያስፖራወች "በቃ" (NO MORE!) አለም አቀፍ እንቅስቃሴ እማኝ ነው፡፡ እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ሚና የጎላ ሊሆን ይገባል፡፡

**የቡድን ውይይት**

1. በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት በተለይ በሳኡዲ አረቢያ ዜጎቻችን ላይ የሚደርሰው አሰቃቂ እና አሳዛኝ እንግልት ለምን መከላከል አልተቻለም? በነዚህ ሀገራት ያሉ ሚሲዮኖቻችን ከሚፈለገው አገልግሎት አንጻር ምን ያህል ተደራጅቷል?
2. የሚከተለውን ሀሳብ በመደገፍ በመንቀፍ ተከራከሩ፡፡ "በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ከኢምበሲዎች/ቆንስላዎች ይልቅ በህገወጥ ደላሎች የታደሰ ፓስፖርት ማግኘት ይቀላል፡፡ ይህ ማለት በነዚህ ሀገራት የኢምበሲዎች/ቆንስላዎች ስራተኞች ስራቸውን በህገወጥ ደላሎች በኩል በፍጥነት ይፈፀማሉ፡፡ ይህ ደግሞ እነዚህ ሰራተኞች በህገወጥ የሰወች ዝውውር መረቦች ውስጥ እጃቸው ሊኖርበት እንደሚችል መገመት ያስችላል"፡፡

### 2.3.5 የውጭ ዕዳ መጨመር እና የፋይናንስ አለመረጋጋት

አሁን ያለው ፈጣን ዓለም አቀፍ እድገት እና ብልጽግና ሀገራት በጋራ ከሚጋሩት የተሳሰረ ኢኮኖሚያዊ እና የፋይናንስ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በትክክለኛው መንግድ የተገኛ የብድር አቅምን በመፍጠር ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ያጋራ የመልማት እድልን ያመጣል፡፡ ሙስና ከገባበት ግን የታለመለትን ዓላማ ስቶ የጥቂቶችን ድንበር ዘለል የሌቦች መረብ አባላትን በማበልጸግ ሀገራዊ ድህነትን ያንሰራፋሉ፡፡ በብድር እና በተለያዩ የሁለትዮሽ ወይም የባለብዙ ዘርፍ አለም አቀፍ ግንኙነቶች የሚገኙ ብድሮች ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለታቀደላቸው አላማ ሳይውሉ በህገ ወጥ መንገድ ከሀገር ይወጣል፤ ልማቱም ሳይለማ የብድር ክፍያ ሀገሪቱ ከአበዳሪ ተቋማትና ሀገራት ትጠየቃለች፡፡ ሀገሪቱም ዕዳ የመክፈል አቅም ስለማይኖራት ከፍተኛ የእዳ ጫና ውስጥ ይዘፍቃታል፡፡ ስለሆንም ሀገሪቱ ተጨማሪ ብድር እና እርዳታ እንዳታገኝ ከማድረግ ባለፈ ባበዳሪ ተቋማትና ሀገራት ተፅዕኖ ስር ትወድቃለች፡፡

የውጭ ብድር ለወሳኝ ፕሮጀክቶች እንደ መሠረተ ልማት፣ ጤና አጠባበቅ ወይም ትምህርት እንዲውሉ የታቀዱ ገንዘቦች በሙስና ምክኒያት ወዳልታቀዱና አስፈላጊ ላልሆኑ ፕሮጀክቶች

ሊዛወሩ ይችላሉ፤ ከዚያም አልፎ ገንዘቡ በቀጥታ ወደ ሙሰኛ ባለስልጣናትና ተባባሪዎቻቸው የግል ኪስ ይገባል። ይህም የሀገሪቱን የመልማት ፍላጎትና የኢኮኖሚ ዕድገትን ያኮስሳል። ሙሰኛ ባለሥልጣኖች ከአበዳሪ ሀገራት ወይም ተቋማት ጋር በሚደራደሩበት ወቅት በአበዳሪዎች በጥቅም በመደለል ሀገሪቱን ሊጎዳ የሚችልና አበዳሪወችን ብቻ በሚጠቅም ውል በመስማማት ከዚያም ሲያልፍ የፕሮጀክት ወጪን በመጨመር የዕዳ ጫናን የበለጠ በማባባስ ሀገሪቱን ወደ ዕዳ ቀውስ ሊያስገቧት ይችላሉ። ሀገሪቱ ከፍተኛ የእዳ ጫና ስትገባ ብድር የመመለስ አቅም ስለማይኖራት ተጨማሪ የውጭ ብድር ማግኘት አትችልም። በዚህ ምክኒያት በሀገር ዉስጥ የኑሮ ውድነትን ያባብሳል፤ ህዝቡ በተቋማት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል፣ ታማኝ ኢንቨስተሮችን ተስፋ ያስቆርጣል፣ የፋይናንስ አለመረጋጋት ይፈጥራል፣ ይህም የረጅም ጊዜ የልማት ግቦችን ለማሳካት የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ ያደርገዋል።

**አስረጅ ናሙና**

*በማሌዥያ ያለው የ1MDB የሙስና ቅሌት በማደግ ላይ ያለች ሀገርን እንዴት እንደሚያዳክም ትልቅ ምሳሌ ሆኖ ያገለግላል። Malaysia Development Fund Bhd (1MDB)፣ በመንግስት የሚመራ የስትራቴጂክ ልማት ኩባንያ፣ ውስብስብ በሆነ የሼል ኩባንያዎች ብድር እና አጠራጣሪ ግብይቶች ውስጥ ተካፍሏል ይህም የብድር ፈንድ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር አላግባብ መዘበረ። ይህ ቅሌት በማሌዢያ ላይ ከፍተኛ የእዳ ጫና ከማስከተሉም በላይ የሀገሪቱን ስም በማጉደፍ የኢንቨስተሮችን እምነት በመንካት ለፖለቲካዊ አለመረጋጋት አስተዋጽኦ አድርጓል። የተዘረፈውን ገንዘብ ለማስመለስ እየተካሄደ ያለው የህግ ትግል ሙስና የሚያስከትለውን ዘላቂ ጉዳት እና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ያሳያል።[2]*

[2] Hannah Ellis-Petersen (2020) https://www.theguardian.com/world/2018/oct/25/1mdb-scandal-explained-a-tale-of-malaysias-missing-billions

### 2.3.6 ሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች መስፋፋት

የአፍሪካ ቀንድ አስኳል እንደ መሆኗ፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የጸጥታ ችግር ያለበትን የቀጠና አውድ ያገናዘበ የውጭ ጉዳይ እና ብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲዎችና ስልቶች ትከትላለች። ቀጠናው አልሸባብን የመሳሳሉ አሸባሪ ቡድኖች የሚንቀሳቀሱበት እና ለድንበር ተሻጋሪ የወንጀል መረቦች እንቅስቃሴ እድል የሚፈጥር ስለሆነ ሀገራችን ዘወትር ንቁ የሆነ እና ከሙስና የጸዳ ተቋማት ያስፈልጓታል።በተጨማሪም እጅግ ወሳኝ የሆነው የቀይ ባህር የውሃ ላይ ዓለም አቀፍ የንግድ ቀጠና ያለበትና ከፍተኛ  ህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የጦር መሳሪያ ዝውውር እና ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር የተንሰራፈበት ስለሆነ ለሀገራችን ተጨማሪ ተግዳሮቶች ይፈጥራሉ።

ኢትዮጵያ ህገወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ካለባቸው የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ስትሆን ሙሉበሙሉ በሚባል ደረጃ የጦር መሳሪያወቹ የጎረቤት ሀገራትን ድንበር ተሻግረው ነው የሚገቡት። በዚህ የዝውውር ሰንሰለት የጸጥታና የደህንነት ሰዎች፤ በተለያየ የስልጣን ተዋረድ ያሉ የመንግስት የስራ ሀላፊዎች፤ ህገወጥ ነጋዴዎችና ሌሎችም ህገወጥ አካላት ተዋናዮች እንድሆኑ ይነገራል። በዚህ መልክ የሚገቡ የጦር መሳሪያወች ለሀገር ሰላም እና መረጋጋት ዋነኛ ጠንቅ እየሆኑ መጠዋል።

በተለይ በዘርፍ ዉስጥ በህገወጥ መንገድ ሀላፊነት ባልተሰጣቸውና በማይመለከታቸው የተቋሙ ሰራተኞች  ሰነዶች ተሰርተውና ትክክለኛ እንደሆኑ በማስመሰል ማረጋጫ የመስጠት ጉዳይ እንዳለ መረጃወች ያመለክታሉ። ይህ ድርጊት ለተዳራጁ አደገኛና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀለኛ ቡድኖች፤ ሽብርተኞችና ህገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።ይህንን አደገኛ ኔትወርክ ለመቆጣጠር ኢትዮጵያ ከሌሎች ጎርቤቶቿና ሀገሮች እንዲሁም ከሚመለከታቸው አለም አቀፍ ተቋማት ጋር መረጃ በመለዋወጥና በመተባበር ጉዳቱን መቀነስ ይቻላል። የዲፕሎማቲክ ተቋሞቻችንም ዋነኛ ተግባር ሊሆን ይገባል።

አብዛኛዎቹን ችግሮች ሀገራችን መቋቋም የቻለች ቢሆንም፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ምክንያት የበርካታ ዜጎቻችን ለአደጋ ሰለባ ከመሆን ማዳን አልተቻለም። የሚሲዮኖቻችንን አቅም አጎልብቶ እና ምግባረ ብልሹ ከሆኑ ሰራተኞች ከማስተካከል እኩል ጎረቤት ሀገራት ከተፈጠሩት አደጋዎችም በመማር የውጭ ጉዳይ እና የጸጥታ ዘርፋችንን በዘላቂነት ከሙስና አደጋ መጠበቅ አለብን። ለምሳሌ፦በፈረንጆቹ 2013 አልሸባብ በናይሮቢ የሚገኘዉን ታዋቂዉን የዌስት ጌት የገበያ ማእከል ያጠቁት የቡድኑ አባላት

የጸጥታ አካላትንና ሌሎችንም በጉቦ(ብራይብ) በመደለል ያቀዱትን የጥፋት እርምጃ እንዲያሳኩ አግዟቸዋል፤ በጥቃቱም ከ60 በላይ ንጹሀን ሰወች ተገድለዋል (ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል 2014)። እንዲህ ዓይነቱ አደጋ መቸም እንዳይከሰት እና ብሄራዊ ደህንነታችንን አደጋ ውስጥ እንዳይከት ሙስና መከላከል ተልዕኮ እጅግ ወሳኝነት አለው።

**የቡድን ውይይት**

1. ኢትዮጵያ ካለችበት ጅዖፖለቲካዊ ቀጠና አንጻር እና የአፍሪካ የድፕሎማሲ መዲና በመሆኑዋ በድፕሎማሲ ካባ ተሸፍነው ህገ ወጥ የሰዎች፣ አዳንዛዥ ዕጽ፣ የገንዘብ እና መሰል ህገ ወጥ ንግድ ላይ የተሰማሩ ተዋንያን ለመከላከል የምትከተለው ስልቶች እና ዘዴዎች የዚህን ዘርፍ ሙስና በዘላቂነት መከላከል ስለ መቻሉ ወይም ያለመቻሉን ይከራከሩ።

**የምዕራፍ ማጠቃለያ**

በዚህ መዕራፍ መጀመሪያው ክፍል ሙስና ስጋት አንድ ተቋም ዓላማ እንዳይሳካ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትል ቀጣይነት ያለው ውስጣዊና ውጫዊ ክስተት እንደ ሆነ በስፋት ቀርቧል። በተቋማት ውስጥ ለተለያዩ የብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ለሙስና የመጋለጥ እድላቸውን ከፍ ያደርገዋል። ከነዚህም ለሙስና ስጋት ከሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮች ውስጥ አንዱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በበቂ ሁኔታ በሰው ሃይልና በቁሳቁስ አለመደራጀቱ ነው። የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በቅንነት፣ በታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ሃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው ደግሞ በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት እንዲጨምር የሚያድርጉ ተጨማሪ የአሰራርና የሥነምግባር ጉድለቶች ናቸው።

በሁለተኛው ክፍል በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚከሰት ሙስና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶችን ተዳሷል። በመጀመሪያው ክፍል ሙስና እንዴት የሀገርን ገፅታ በማበላሸት ዓለም አቀፋዊ ተጽዕኖ እና ተሰሚነት እንደ ሚቀንስ ተወያይታቿል። በክፍል ሁላት ሙስና እንዴት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች እና የልማት ትብብሮችን ሊያሸሽ እንደምችል አይተናል። በቀጣዩ ክፍል በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ዳያስፖራው በሙስና ምክንያት ያሚደርሲባቸውን ጉዳት ተወያይተናል። በክፍል አራት ሙስና የውጭ ዕዳን በመጨመር እና የፋይናንስ ያላመረጋጋት በማምጣት እንዴት ሉዓላዊ የፖሊሲ ነጻነትን እንድሚጎዳ ተመላክቷል። ክፍል አምስት ሙስና

ሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች እንዲስፋፉ እንዴት መንገድ እንደሚከፍት እና ብሄራዊ ደህንነታችንና ጥቅሞቻችን ለአደጋ እንደሚያጋልጡ ተወያይተናል።

***ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች***

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለማሳየት 0 - 3 ያለውን ነጥብ በመጠቀምና (√) ምልክተ በማስቀመጥ ምን ያህል እንደተረዳችሁ አሳዩ። በዚህም መሰረት 3=ከፍተኛ መረዳት ፤ 2= መካከለኛ መረዳት ፤ 1=ዝቅተኛ መረዳት ፤ 0 = ሙሉ በሙሉ አለመረዳትን የሚወክሉ ይሆናሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ጥያቄዎች | የግንዛቤማመሳከሪያ ነጥቦች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 1. | የሙስና ስጋቶች በማንኛውም ተቋም በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙና የሚኖር መሆኑን ተረድቻለሁ | | | | |
| 2 | በተቋማችን ውስጥ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ያሉ የሙስና ስጋቶች መኖራቸው በሚገባ መገንዘብ ችያለሁ | | | | |
| 3 | በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚስተዋሉ የብልሹ አሰራሮችና ዋና ዋና የሙስና ስጋቶች መለየት ችያለሁ | | | | |
| 4 | የሙስና ስጋቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመለየትና በመተንተን የሙስና ስጋት መከሰት ዕድሎችን እና ሊፈጠሩ የሚችሉ ኪሳራዎች መቀነስ እንድሚቻል ተረድቻለሁ። | | | | |
| 5 | የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በቅንነት፣ በታማኝነት፣ በገለልተኝነት፣ በተጠያቂነት እና በግልፅነት በመስራት የሙስና ስጋቶች መቀነስ እንደሚችሉ ተረድቻለሁ። | | | | |
| 6 | ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል አንዱ የሥነምግባር ደንብ ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ መሆኑን ተረድቻለሁ። | | | | |
| 7 | ግልፅነት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ በሚገባ በመስጠት ለሙስና የመጋለጥ እድልን እንደሚቀንስ ተረድቻለሁ | | | | |
| 8 | አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሙስናን ለመዋጋት ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተረድቻለሁ። | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰውናንብረት አስተዳደር ስርአት መኖር ለሙስና አደጋ የመጋለጥ እድልን እንደሚቀንስ ተረድቻለሁ፡፡ | | | | |
| 10 | የሃብት ምዝገባ ሥርዓት መኖር ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል እንደሚያስችል ተረድቻለሁ | | | | |
| 11 | በተቋማት ውስጥ ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መኖር ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችና ሙስና በእጅጉ እንደሚቀንስ መረዳት ችያለሁ፡፡ | | | | |
| 12 | በተቋማችን ያሉትን መካከለኛ እና ከፍተኛ የሙስና ተጋላጭነት ያለባቸውን አሠራሮችን ለይቻለሁ | | | | |
| 13 | ሙስና የሀገር ገጽታ ላይ የሚያስከትለውን ዋና ጉዳቶችን ተረድቻለሁ | | | | |
| 14 | ሙስና ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች እና የልማት ትብብሮችን ሊያሸሽ እንደ ሚችል የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎችን ማቅረብ እችላለሁ | | | | |
| 15 | ሙስና ዳያስፖራው የሚገባቸውን እርዳታ ከኢትዮጵያ ሚሲዮኖች እንዳያገኙና መብታቸው ተገቢውን ክብር እንዳያገኙ ሙስና እንዴት አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ማስረዳት እችላለሁ | | | | |
| 16 | ሙስና የውጭ ዕዳን በመጨመር እና የፋይናንስ ያላመረጋጋት በማምጣት እንዴት ሉዓላዊ የፖሊሲ ነጻነትን እንድሚጎዳ መተንተን እችላልሁ፡፡ | | | | |
| 17 | ሙስናሽብርተኝነት እና ድንበር-ዘለል የተደራጁ ወንጀሎች እንዲስፋፉ እንዴት መንገድ እንደሚከፍት ተረድቻለሁ | | | | |
| 18 | ሙስና ብሄራዊ ደህንነትንና ሀገራዊ ህልውናን ለአደጋ እንዲጋለጥ ማስረዳት ችያለሁ | | | | |

## ምዕራፍ ሶስት

# 3. በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና መከላከያ ስልቶች

### 3.3 መግቢያ

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው። ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው። ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል። ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል። ችግሩ ከተከሰተ በኂላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል።

እንደሚታወቀው በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚፈጸም ሙስና በአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ዲፕሎማሲ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። የውጭ ኢንቨስትመንትን በመቀነስ፣ የልማት እርዳታን በማዛባትና በሕገ-ወጥ ንግድ እንቅስቃሴዎች በመደገፍ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያደናቅፋል። በፖለቲካም ሙስና ዜጎች በመንግስት ላይ ያላቸዉን እምነት በመሸርሸር ፣ ብልሹ አስተዳደርን በማስፋፋት ዜጎች የተረጋጋ ህይወት እንዳይኖራቸው ያደርጋል። በዲፕሎማሲም በኩልም ሙስና ከሌሎች አገራት ጋር ያለውን ግንኙነት በማበላሸት፣ አለም አቀፍ ትብብርን በማዳከምና አገሪቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝቅ በማድረግ አሉታዊ ምስል ይፈጥራል።

በዘርፉ የሚፈጸም ሙስና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገሪቱ ጥሩ ስም እንዲኖራት በማድረግ የውጭ ኢንቨስትመንትን በመቀነስ፣ የቱሪዝም እንቅስቃሴን በማዳከምና ከሌሎች አገራት ጋር ያለውን ትብብር በማደናቀፍ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህ ደግሞ ባለሀብቶች በሙስና ምክንያት በሚፈጠሩ አለመተማመን ፣ ግልጽ ባልሆኑ ስምምነቶች እና በብልሹ አስተዳደር ምክንያት

ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እንዳይኖራቸው በማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በኢንቨስትመንት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህ ደግሞ ባለሀብቶች ላይ ስጋትን በመፍጠር አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡና ቀደም ብለው የተደረጉ ኢንቨስትመንቶችም እንዲዳከሙ ያደርጋል።

በተጨማሪም በዘርፉ የሚፈጸም ሙስና ከልማት አጋሮች ጋር ያለውን ትብብር በእጅጉ ይቀንሳል ። ግልጽ ያልሆነ አሰራር፣ ሙስና እና ብልሹ አስተዳደር ከልማት አጋሮች ጋር ያለውን እምነት በማዳከም እርዳታን እንዲቀንስ ወይም እንዲቆም ከማድረጉ ባሻገር ፕሮጀክቶች በጊዜው እንዳይጠናቀቁ እና በብቃት እንዳይተገበሩና በልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ ብክነትን በመፍጠር እና በውጤታማነታቸው በመቀነስ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህ ደግሞ በአገሪቱ ልማት እና እድገት ላይ ከፍተኛ እንቅፋት ስለሚፈጥር በዘርፉ ያለውን ሙስና መከላከል ከልማት አጋሮች ጋር ያለውን ትብብር ለማጠናከር እና ለአገሪቱ ዘላቂ ልማት አስፈላጊ ነው።

በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሚፈጸም ሙስና በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎችን እና የዲያስፖራን ህይወት በተለያዩ መንገዶች ይነካል። ለምሳሌ ፣ በፓስፖርት እና ቪዛ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚፈጸም ሙስና አላስፈላጊ ወጪ እንዲከፍሉ ፣ ረጅም ጊዜ እንዲጠብቁ እና ብዙ ችግሮች እንዲያጋጥማቸው ያደርጋል። በተጨማሪም፣ በውጭ አገር ያሉ ዜጎች አስፈላጊ የሆኑትን የምክር አገልግሎቶችና የህግ እርዳታ ሲፈልጉ ሙስና እንቅፋት በመሆን በውጭ አገር ያሉ ዜጎች ከሀገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር እንዲዳከምና ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ወይም በሀገራቸው ሀብት ማፍራት እንዳይችሉ ስለሚያደርግ ከሀገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ያዳክማል።

በዘርፉ የሚፈጸም ሙስና ለሽብርተኝነትና ለአለም አቀፍ ወንጀሎች መስፋፋትም መንገድ ይከፍታል። ሙስና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀለኞችና ሽብርተኛ ቡድኖች በቀላሉ መሳሪያ እንዲያስገቡ እና እንቅስቃሴያቸውን እንዲያካሂዱ ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር በድንበር ቁጥጥር እና ደህንነት ላይ ክፍተት በመፍጠር ሽብርተኝነትና ወንጀል እንዲበራከት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለሆነም በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ሙስናን መከላከል ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለውጭ ኢንቨስትመንት፣ ለአገሪቱ ጥሩ ስምና ለአጠቃላይ እድገቷ ወሳኝ ነው። በዚህ ምእራፍ ውስጥ

በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶች በስፋት እንደሚከተለው ተዳሰዋል።

በዚህ ምዕራፍ በአጠቃላይ የሙስና መከላከያ ስልቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል። በክፍል አንድ የሙስና መከላከያ ምንነት ተደሷል። በክፍል ሁለት አስተዳደራዊ አሰራርና ውስጣዊ ቀጥጥርን በማጠናከር ሙስናን መከላከል ላይ ትኩራት ያደረጉ አስራ አንድ የሙስና መከላከያ ስልቶች በስፋት ቀርቧል።በክፍል ሶስት የሙስና ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ የሀገራችንንና ሀገራችን ያፀደቀቻቸውን ህጎችን በወፍ በረር ይቃኛቸዋል።

**የምዕራፍ አራት ዓላማዎች**

ሰልጣኞች በዚህ ምዕራፍ የሚሰጠውን ስልጠና ሲያጠናቅቁ፣

- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
- በዘርፉ ውስጥ ያሉ የመከላከለያ ስልቶች ይዘረዝራሉ፣
- የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣
- በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

**የዚህ ምዕራፍ ስልጠና የሚወስደው ግምታዊ ጊዜ**

ስልጠናው 2:30 ሰዓት ሊወስድ ይችላል።

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለ ተሳታፊ ጋር በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ።
2. በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ።
3. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ።

## 3.4 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቅው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ተገቢ ብቁና ልምድ ያላቸውን ዲፕሎማቶች ከመቅጠር ባሻገር በየጊዜዉ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ክፍተት ያለባቸውንም ክፍተቱን በመለየት ተከታታይና ጠንካራ ስልጠና በመስጥት ማብቃት ይቻላል፡፡

## 3.5 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

### 3.5.1 ግልጽነት

ግልጽነት ማለት ዜጎች ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ በቀላል መንገድ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ይህም  ተቋማት እንዴት እንደሚሰሩ፣ ምን ውሳኔዎች እንደሚወስዱ፣ እና ምን ሀብቶች እንደሚያስተዳድሩ በግልጽ ማሳየትን ያካትታል፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ሲኖራቸው፣ የመንግስት አሰራሮች ግልጽ ይሆናሉ፣ እናም በአስተዳደራዊ በደል፣ ብልሹ አሰራር ወይም ሙስና ሰለባ ከመሆን ይታደጋሉ፡፡ እንዲህ ያለው ግልጽነት ዜጎች ተጠያቂነትን እንዲጠይቁ፣ በተቋማት ውስጥ ያለውን ተጠያቂነት ለማሳደግ፣ እና ለተሻለ አስተዳደር አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ዘርፍም  ለህብረተሰቡ የሚሰጣቸውን መንግስታዊ አገልግሎቶች በዝርዝር የሚገልጽ መመሪያ ማዘጋጀትና ለህዝብ ማስተዋወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ መመሪያ ምን አይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ፣ ለማን እንደሚሰጥ፣ ምን መስፈርቶች እንደሚያሟላ እና አገልግሎቱን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል በግልፅ ማብራራት ይኖርበታል፡፡ በዘርፉ ግልጽነት ከሌለ፣ ዜጎች በሚፈልጉት ጊዜና መጠን አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት አይችሉም፡፡ ይህ ደግሞ መብታቸውን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ይፈጥራል፤ እንዲሁም ተጠያቂነትን ማስፈን

አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ግልጽነት በሌለበት ሁኔታ ዜጎች በአስተዳደራዊ በደል፣ በሙስናና በብልሹ አሰራር ሰለባ ለመሆን ይጋለጣሉ፡፡ ስለዚህ ግልጽነት ለተጠያቂነት፣ ለፍትህ እና ለተሻለ አስተዳደር መሰረት ስለሆነ የግልጽነት አሰራር በማስፈን ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል ያስፈልጋል፡፡

### 3.5.2 ተጠያቂነት

ተጠያቂነት ማለት አንድ ሰው ወይም ተቋም ለተሰጣቸው ኃላፊነት ተጠያቂ መሆን እና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ካልተወጡ ለውጤቱ ተጠያቂ መሆን ነው፡፡ ይህም ተግባራቸውን በአግባቡ መፈፀም እና በተፈፀመ ስህተት ምክንያት ለሚደርስ ኪሳራ ወይም ጉዳት ካሳ መክፈልን ሊያካትት ይችላል፡፡ የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራሀም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ተጠያቂነት ለማስፈን ውስጣዊ እና ውጫዊ ዘዴዎች መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ውስጣዊ ተጠያቂነት ለማስፈን በዘርፍ ውስጥ ያሉ አሰራሮችን፣ ደንቦችን እና እሴቶችን በአግባቡ በመተግበር እና ስራዎችን በመከታተል እና በመቆጣጠር መከላከል ሲሆን ይህም በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ ኃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብን፣ ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን፣ እና የውስጥ ኦዲት እና ግምገማዎችን ማካሄድን ያካትታል፡፡

በሌላ መልኩ ውጫዊ ተጠያቂነትን ለማስፈን ደግሞ ዘርፍ ለህግ አውጪ አካላት፣ ለፍርድ ቤቶች፣ እና ለህዝብ ተጠያቂ መሆንን ያካትታል፡፡ ይህም ለህግ አውጪ አካላት ሪፖርት ማቅረብ፣ ለህዝብ መረጃ መስጠት፣ እና ለህዝብ ቅሬታዎች ምላሽ መስጠትን ያካትታል፡፡ ተጠያቂነት በአጠቃላይ መንግስት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአግባቡ በመስራት እና ህብረተሰቡን በታማኝነት በማገልገል ይገለጻል፡፡ የተጠያቂነት ስርዓት በአግባቡ ሲሰራ ብልሹ አሰራርን እና ሙስናን ለመከላከል ይረዳል፡፡

ከግልጽነትና ተጠያቂነት ጋር ተያይዞ ዘርፍ በሚሲዮኖቻችን ለቢሮ አገልግሎት፣ ለሚከራዩና ለመኖሪያ አገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች ሲገነቡ/ሲታደሱ ለሚያዙ ውሎች ለሙስና የመጋለጥ አዝማሚያዎች ስላሉ በሂደቱና ስራው እስኪጠናቀቅ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር አሰራር በማስፈን ብልሹ አሰራርን እና ሙስናን መከላከል ያስፈልጋል፡፡

## 3.6 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡

የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

## 3.7 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡

የውጭ ጉዳይ ዘርፍም ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚውሉ ውጤታማ ስልቶች አንዱ፣ የመንግስት ሰራተኞችና ኃላፊዎች ንብረታቸውን በግልፅ እንዲገልጹና እንዲመዘግቡ ማድረግ ነው። ይህ ስርዓት ህጋዊ ያልሆነ እና ምንጩ ያልታወቀ ንብረት መኖሩን ለመለየት እና በሙስና ወይም በሌሎች ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች የተገኘ ንብረት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡና ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በማሳደግ ሙስናን ለመዋጋት ይረዳል።

### 3.8 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ውስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፣ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው።

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል። በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል።

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል። በተለይ የዲፕሎማቲክ ከለላን በመጠቀም ዲፕሎማቶችና ቤተሰቦቻቸው በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ የሰዎች ዝውውር፣ ህገወጥ ንግድና የአደገኛ እጽ ዝውውርና ለሌልች የግል ጥቅም ማካበቻ እንዳይሳተፍ ተቋሙ ከፍተኛ ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

## 3.9 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

በውጭ ጉዳይ ዘርፍም ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና የፀረ-ሙስና ትግል ዘላቂ እና ቀጣይነት ያለው ሂደት ሲሆን ተቋማት ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዘርፍ ያሉ ተቋማት የፀረ-ሙስና ትግልን በእቅዳቸው፣ በዕለታዊ ስራቸው፣ በሪፖርት አሰጣጥና በውጤት ግምገማ ሂደታቸው ውስጥ በማዋሃድ ይኖርባቸዋል፡፡ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የፀረ-ሙስና ትግልን እንደ ዋና አጀንዳ በማድረግ በተቋሙ ውስጥ ያለውን ማህበረሰብ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በተሳትፎ እንዲሰሩ ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

## 3.10 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቻ ሙሽናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- ☑ በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ☑ ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ☑ ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- ☑ የጥቅም ግጭትን የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣

- ☑ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- ☑ በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- ☑ በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

በዚህም መሰረት በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ያሉ የተቋማት አመራሮችም በተቋማቸው ውስጥ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና አሉአቸው:: ስለሆነም እነዚህ የዘርፍ አመራሮች ራሳቸውን የመልካም ስነምግባር አርአያ በማድረግ፣ በተቋማት ውስጥ ስነምግባራዊ አመራርን በመተግበር፣ ሙስናን ለመከላከል ስራዎችን በማዋሃድ፣ ስነምግባራዊ ባህል እንዲሰፍን በማድረግ፣ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ስትራቴጂዎችን በመንደፍና በመተግበር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን በማውጣትና በመተግበር፣ ሙስናን የሚያመቻቹ የአሰራር ሂደቶችን በማሻሻል፣ እና በስነምግባርና በአገልግሎት አሰጣጥ ብቃታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን በመሸለም ሙስናን ለመዋጋት ንቁ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል::

### 3.11 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው:: ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው:: ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል:: እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል:: የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ከሌሎች ሀገራትና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር ስለሆነ አብዛኛው ግንኙነቱ ከነዚህ ተቋማትና ሀገራት ጋር በትብብር ካልሰራ ድንበር ተሻጋሪ የሙስና ወንጀልን መታገል አዳጋች ይሆናል::

### 3.12 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው:: ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ

ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

**ማጠቃለያ፡**

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

**የማጠቃለያ ጥያቄ**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
2. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂ መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኖቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡

3. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡
4. በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2010)፡፡ የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ 699/2010፡፡ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ፣ አዲስ አበባ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2013)፡፡ ፌዴራላዊ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ፡፡ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አበባ፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፡፡ የተሻሻለው የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/97፡፡ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015)፡፡ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ግምገማዊ ጥናት፡፡የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015 ) ፡፡ የሙስና ጽንሰ ሀሳብ እና የመከላከያ ስልቶች ማስልጠኛ ሞጁል፡፡ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2014)፡፡ የሙስና ስጋት የዳሰሳ ጥናት በኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ፡፡ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2014)፡፡ በፍርድ ቤቶች የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2014)፡፡ የትምህርት ሴክተር የሙስና ስጋት ጥናት፡፡ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፡፡ አዲስ አበባ ፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2014) ፡፡ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት ስልጠና ሞጁል፡፡ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣አዲስ አበባ ፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2002)፡፡ ሳይቃጠል በቅጠል፣ ምእራፍ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2001)፡፡ ሥነምግባር እና ሙስና (የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ)፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2001)፡፡ ሥነምግባር እና ሙስና (የስልጠና ሞጁሎች)፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2003) ፡፡ፕሮፍይል፣ ምእራፍ ማተሚያ ቤት ፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (1997)፡፡ የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ አዋጅ ቁጥር (434/97)፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2007)፡፡ የሙስና ወንጀልችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር (881/2007)፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አበባ፡፡

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (1999)፡፡ የፀረ-ሙስና ኮንቬሽን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 544/1999፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አበባ፡፡

የአፍሪካ ሕብረት የፀረ-ሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን(2007)፡፡ AUCAC 545/2007

የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ (1993)

African Union (2006), "*African Union Convention on Preventing and Combating Corruption*." Maputo

Black's Law Dictionary (1990) 6th Ed. St Minn. Westpublishing.

FDRE (2015). The Revised Anti-corruption Special Procedures and Rules of Evidence (amendment) Proclamation, 882/2015. Addis Ababa .

FDRE(2010). The Diclosure and Registration of Assets proclamation, 668/2010. Addis Ababa.

Hannah Ellis-Petersen (2020) https://www.theguardian.com/world/2018/oct/25/1mdb-scandal-explained-a-tale-of-malaysias-missing-billions

Kato, Damian (1995*). Enhancing of ethics, Transparency and Accountability in Uganda*. Workshop on civil service reform in Anglophone Africa. Cape Town(Unpublished).

Lauren del Valle, Kara Scannell, Sabrina Souza, Nicki Brown and Gregory Krieg, (July 2024) https://edition.cnn.com/2024/07/16/politics/bob-menendez-verdict/index.html

The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission (2015)::The FEAC Annual Performance Report, 2015 Budget Year, Addis Ababa.)

Transparency International (2008).TI Bribe Payers Index 2008. Periodic survey report, TI, Berlin. http://archive.transparency.org/policy_research/surveys_indices/bpi/bpi_2008.

Transparency Ethiopia (2008) *Corruption Diagnostic Baseline Survey Report*. Transparency Ethiopia, Addis Ababa

Transparency International (2022). *Corruption Perception Index 2021*. Transparency International.

Transparency International. (2018). *How Do You Define Corruption?* Retrieved from What is Corruption?:https://www.transparency.org/what-iscorruption#

Transparency International. (2019). Corruption Perception Index. Transparency International.

World Bank (2014). *World Bank Global Integrity Report*. The World Bank: Washington D.C.

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION
ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et

**ሥነ-ምግባራዊ አመራርነት ለተቋማዊ ተልዕኮ ስኬት!**